# የትውን እና የእይታ ጥበባት

## የመምህሩ መምሪያ

## 4ኛ ክፍል


**አዘጋጅ ፡**

ምህረቱ ዋሴ

ታሪኳ ተሰማ

ታምራት አብርሃም

**አርታኢ፡**

ፍላጎት ታደሰ

**ሰዓሊ፡**

ምህረቱ ዋሴ

**የሙዚቃ ኖታ ጸሐፊ፡**

ታሪኳ ተሰማ

**ጥራት ገምጋሚ፡**

ተክለማሪያም ጥላሁን

ተዋበ ታደሰ

**አጽዳቂዎች፡**

ሜላት መካሻ

ፍቅሩ አርፋሶ

አሰጋኸኝ ጉየ

አረጋ አሰፋ

ሰውነት ቶማስ

ለምለም ደግፌ



ሰኔ- 2014 ዓ.ም

**መግቢያ**

በዚህ የአራተኛ ክፍል የእይታ እና የትውን ጥበባት መጽሀፍ ተማሪዎች ስለ ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት በቂ ግንዛቤ እና ችሎታ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል:: ይህ መጽሀፍ በአምስት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን በውስጡም ስለ ስነ-ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት በስፋት እና በጥራት ትንታኔ ከመስጠት በተጨማሪ በቂ ክህሎት እንዲያገኙ የተግባር ስራዎችን አካቶ የያዘ ነው:: በዋናነት የማየት ፣ የፈጠራ ችሎታን የማሳደግ ፣ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የማገናኘት እና ከአካባቢያዊ እውቀቶች ጋር በማዛመድ ሙያዊ ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ ታሳቢ ሆኖ የተዘጋጀ መጽሀፍ ነው:: ተማሪዎች ይህንን የአራተኛ ክፍል መጽሀፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ የሚከተሉትን የብቃት አሀዶች ያገኛሉ፦

- ዝርግና ባለ ሶስት አውታር ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ይስላሉ ፣ የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ ሩብ ኖታ ድረስ ይገልፃሉ
- ድምጽ-አልባ ትወናዎችን ፣ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይከውናሉ
- የቁምና አግዳሚ ፎቶ ግራፍ አነሳስ አይነቶችን ያብራራሉ
- ተንቀሳቃሽ ምስሎችንና ፎቶዎችን በመመልከት መልዕክቶችን ይረዳሉ
- በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ የሙዚቃ ጽሁፍን (መስመርንና ክፍት ቦታን) ከቁልፍ የኖታዎች ቦታ ጋር በማገናኘት (የረዳት መስመሮችን በማካተት) ይረዳሉ
- የቤተሰብ የአብነት እንቅስቃሴዎችን በዘፈንና በውዝዋዜ ያሳያሉ
- ንድፎችን በመስራት የተለያዩ ቀለሞችን በመቀባትና በኮላጅ መልክ በመለጠፍ ይለማመዳሉ
- ሃገር በቀል የቤት አሰራርን ፣ ማስጌጥንና የሙዚቃ ጨዋታዎችን ያውቃሉ ፣ ያደንቃሉ

- በድምፅ-አልባ ተውኔትና በግለ-ተውኔት(መነባንብ) ፣ እንዲሁም በስዕልና በፎቶ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ
- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያዛምዳሉ
- የመዝሙሮችን ፣ የዝርግ ቅርጾችንና የቀለማትን አስፈላጊነት ይረዳሉ
- ከዛፎችና እንስሳት እንቅስቃሴ በመነሳት ውዝዋዜዎችን ያስመስላሉ

## የገጽ ማውጫ

ምዕራፍ አንድ....2
1. ምልከታ....2
1.1 መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት....4
1.2. ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት....11
1.2.2. ዝርግ ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት....15
1.3. ምጥን ተውኔቶችን መረዳት....18
1.4. የቁምና አግዳሚ ፎቶግራፍ አነሳስ አይነቶችን መረዳት....20
1.4.1. መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያን....22
1.4.3. ፎቶዎችን በመመልከት መልዕክቶችን መረዳት....28
ምዕራፍ ሁለት....34
2. የግልና የቡድን ትግበራዎች....34
ለምዕራፉ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 28....34
2.1. የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ እና ቁልፎች....36
2.2. ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎች....43
2.2.1. የቤተሰብ የአብነት እንቅስቃሴዎችን በመዝሙር እና በውዝዋዜ ማሳየት....45
2.3. ኮላጅን ለስላሳ/ሸካራ በሆኑ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች መስራት....48
2.4. ቅርፆች፤ ለስላሳነትና ሸካራነት....52
2.5. ድምፅ-አልባ ተውኔትና ግለ-ተውኔት (መነባንብ)....55
2.5.1. ድራማዊ መነባንብ....57
2.5.2. ተውኔቶችን ለተመልካች ማቅረብ....58
ምዕራፍ ሶስት....62
3.የትውን እና የእይታ ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ....62
3.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በማህበረሰቡ ታሪክና ባህል ያለው ሚና....64
3.1.1. የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ጠቀሜታ....66
3.1.2. ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ....77
3.1.3. የትውን ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ....82
ምዕራፍ አራት....85
4.አድናቂነት....85
4.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በአፈፃፀምና በምስል ጥበባት ውስጥ የመለማመድ ውጤት....87

4.1.1. የእይታ ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ ........ 89
4.1.2. የትውን ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ ........ 91
4.1.3. መዝሙርን እና ውዝዋዜን ደጋግሞ የመለማመድ ውጤት ........ 94
4.2. ሀገር በቀል የቤት አሰራርን እና ማስጌጥን ፣ የሙዚቃ ጨዋታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት ........ 95
4.2.1. ሀገር በቀል የሙዚቃ ጫወታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት ........ 104
ምዕራፍ ........ 108
አምስት ........ 108
5.የትውን እና እይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማዛመድ ........ 108
5.1. የአይታና የትውን ጥበባት እርስ በርስ ያላቸው ዝምድና ........ 110
5.2. የእይታና የትውን ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማገናኘት ........ 111
5.2.1. ዝርግ ቅርፆችን ፣ ቅርፆችን እና ቀለማትን ከሒሳብና ሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማዛመድ ........ 113
5.2.3. የእይታ ጥበብ ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ዝምድና ........ 119
5.2.3. የትውን ጥበባት ከሌሎች ይትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ዝምድና ........ 121
ሐ. ተማሪዎች በየቀኑ የሚያደጓቸውን ድርጊቶች በመዝሙር መግለጽ ........ 132
መ. ስለ አካባቢያዊ ቀለማት፣ ዕጽዋትና እንስሳት መዘመር ........ 136
ዋቢ መጽሀፍት ........ 142

| ምዕራፍ አንድ | 1. ምልከታ<br>ለምዕራፉ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 24 |
|---|---|

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች አካባቢያቸውን በደንብ እንዲመለከቱ እና ለተለያዩ ፈጠራዎች መነሻ ሃሳብ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል:: ተፈጥሯዊ ነገሮችን በመመልከት የተራራዎችንና የዛፎችን እንቅስቃሴዎች ፣ የአበቦችን ቀለማት ፣ የወንዞችና የፏፏቴዎችን ድምፅ ፣ የእንሥሣት አይነቶችንና ባህሪያትን ከትውን እና የእይታ ጥበባት ጋር በማዛመድ ለተለያዩ ፈጠራዎች መነሻ እንዲሆን አካባቢን ማወቅ ትልቅ ሚና ይኖረዋል:: አካባቢያችንን በሚገባ በተረዳን ቁጥር ለሰዕል ፣ ለሙዚቃ ፣ ለቲያትር ፣ ለድርሰት እንዲሁም ለሌሎች የፈጠራ ውጤቶች ጥሩ ግብዓቶችን እናገኛለን:: በዓለም ላይ እጅግ ተፅዕኖ ፈጣሪ የምንላቸው ሰዎች የሰሯቸው ፈጠራዊ ስራዎች መነሻቸው ተፈጥሯዊ ነገሮች ናቸው:: ለምሳሌ አውሮፕላን ከወፎች እንቅስቃሴ በመነሳት ፣ መኪና ባለ አራት እግር እንስሳትን በመመልከት እንዲሁም ባቡር የተለያዩ በደረታቸው የሚሳቡ እንሥሣትን መሰረት በማድረግ የተሰሩ የፈጠራ ስራዎች ናቸው:: ስለዚህ አካባቢያችንን የበለጠ በተረዳንና ባወቅን መጠን የተለያዩ ችግር ፈቺ ምርምሮችን ለመስራት የመነሻ ሃሳብ እናገኛለን::

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ዝርግና ባለ ሶስት አውታር ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ይስላሉ
- የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ ሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ ይገልፃሉ
- ድምጽ-አልባ ትወናዎችን ፣ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይከውናሉ
- የቁምና አግዳሚ ፎቶግራፍ አነሳስ አይነቶችን ያብራራሉ
- በቀላል ምት መዝሙርን እና ውዝዋዜን መዘመር እና መወዛወዝን ይረዳሉ

## የመማር ማስተማር ግብዓቶች

- የመለማመጃ አዳራሽ/ክፍል
- ከበሮ
- ምስል፤ሙዚቃ፤ የተንቀሳቃሽ ምስል ማጫዎቻዎች
- የድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስል መሳሪያዎች

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ተማሪዎችን የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ ሩብ ኖታ ድረስ እንዲገልፁ ማድረግ
- ስለ ቁም እና አግዳሚ ፎቶግራፎች በቂ ማብራሪያ ማድረግ
- ድምጽ አልባ ኖታዎችን በክፍል ውስጥ በተገባር ማሳየት
- ዝርግ ቅርፆችን ቀለም በመቀባት እንዲለማመዱ ማድረግ

## የግምገማና ክትትል ስልት

- በምልከታ
- በግላዊ ገለፃ

- በቡድን ገለፃ

## 1.1 መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

**መግቢያ**

በዚህ ርዕስ መምህሩ ተማሪዎችን በቀላሉ መዝሙሮችን እና ቀላል ምቶችን በመጠቀም እንዲዘምሩ ያደርጋል፡፡ መዝሙሮችን በቀላል ምቶች ለመረዳት ተማሪዎች የተለያዩ ኖታዎችን በቀላሉ ለይተው መዝሙሮችን መዘመር እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህም መዝሙሮችን በቀላሉ በአካባቢያችን ከሚገኙ የተፈጥሮ እንቅስቃሴዎች ጋር ማገናኘት ተገቢ ነው፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ተማሪዎች መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች ይረዳሉ
- የተለያዩ አከባቢዎች ላይ በቀላል ስልተ-ምቶች የሚዘመሩ መዝሙሮች እና ውዝዋዜዎችን ለይተው ይገነዘባሉ

**ማነቃቂያ**

- የምታውቁትን መዝሙር በማጨብጨብ ዘምሩ፡፡

**ፍንጭ**

- የሚዘምሩትን መዝሙር እያጨበጨቡ መዘመራቸውን ያረጋግጡ፡፡

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ተማሪዎችን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጉ
- ስለዘመሩት መዝሙር ማብራሪያ እንዲሰጡ ያድርጉ

- በቡድን ሆነው ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ

***ጠቃሚ መረጃ***

***ሀ. መዝሙሮችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት***


በአከባቢያችን በቀላሉ ልናያቸው ወይም ልንሰማቸው እንዲሁም ደግሞ በትምህርት ቤቶችና በሀይማኖት ተቋማት በቀላል ስልተ-ምቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን ልንሰማቸውና ልናያቸው እንደምንችል መምህሩ ተማሪዎችን በሚገባ ያስረዳሉ፡፡

**ምሳሌ1.1**

<u>**ጭል ጭል**</u>

ጭል ጭል ጭል ጭል
ትንሿ ኮኮብ ይደንቀኛል አንቺን ሳስብ
ከፍ ብለሽ ከዓለም በላይ
ልክ እንደ እንቁ በሰማይ ላይ
ጭል ጭል ጭል ጭል
ትንሿ ኮኮብ ይደንቀኛል አንቺን ሳስብ

ምሳሌ፡- ጭል ጭል




ምስል 1.1- ጭል ጭል መዝሙር በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ

**ለመምህሩ፦**

- ተማሪዎች የተለያዩ በአከባቢያቸው በቀላል ስልተ-ምቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ያድርጉ። በተጫማሪም ከላይ የተጠቀሱትን መዝሙሮች በትልቅ ወረቀት ላይ በመሳል ግድግዳ ላይ በመለጠፍ ተማሪዎችን እንዲዘምሩ ያድርጉ።

## ለ. ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች መረዳት

- ውዝዋዜን በቀላል ስልተ-ምቶች ልንረዳ የምንችለው በምንጫወትበት ጊዜ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ መዝሙር በምንዘምርበት ጊዜም

እንቅስቃሴዎችን በማድረግና በመወዛወዝ መሆኑን ለተማሪዎች ያስረዱ::

**ምሳሌ 1.2**

<u>**ልጅ ለመፈለግ**</u>

**ልጅ ለመፈለግ መተናል ዛሬ በማለዳ**

**ማንን ትፈልጋላችሁ ዛሬ በማለዳ**

**ሃናን እንፈልጋታለን ዛሬ በማለዳ**
**እሷን መቶ የሚወስዳት ማን ጎበዝ አለና**
**ሩት ጎበዝ አለችን**
**የኛ ልጅ በርች በርች እንዳትረች**
**የኛ ልጅ በርታ በርታ እንዳትረታ**

**መልመጃ 1.1**

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ እንስሳቶችና እፅዋቶች እንቅስቃሴ በመነሳት የተለያዩ ውዝዋዜዎችን በቀላል ስልተ-ምቶች እየተወዛወዛችሁ ተለማመዱ::

ፍንጭ

መምህር እንደዚህ አይነት በቀላል ምቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን ተማሪዎች በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያግዟቸው::

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎች መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን ሲያቀርቡ በመመልከት እና ግብረ-መልስ በመስጠት ይገመግማሉ::

### 1.1.1. የሙዚቃ ኖታዎች እስከ ሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ ያሉ ምልክቶች

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ ይገነዘባሉ። ምልክቶችን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ቀላል ስልተ-ምቶችን ይረዳሉ። በዚህም መሰረት መምህሩ የኖታ እና የእረፍት ምልክቶችን በመለየት ያስረዳሉ።

**ማነቃቂያ**

- የምታውቁትን መዝሙር በማጨብጨብ ዘምሩ።


**ፍንጭ**

- ሲያጨበጭቡ የመዝሙሩን ጊዜ ቆይታ መጠበቃቸውን ማረጋገጥ።

**ጠቃሚ መረጃ**

የሙዚቃ ኖታዎች እና እረፍቶች ማለትም ሙሉ ኖታ (4 ምት በድምጽ) ፣ ግማሽ ኖታ (2 ምት በድምጽ) ፣ ሩብ ኖታ (1 ምት በድምጽ) የጊዜ ቆይታ አላቸው። የኖታ እና የእረፍት የጊዜ ቆይታቸውም ተመሳሳይ ነው እነዚህም እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።


| የኖታው ስም | የኖታ (የድምፅ) ምልክት | የእረፍት (ድምፅ-አልባ) ምልክት | የጊዜ ቆይታቸው |
|---|---|---|---|
| ሙሉ ኖታ | 𝅝 | 𝄻 | 4 |
| ግማሽ ኖታ | 𝅗𝅥 | 𝄼 | 2 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ሩብ ኖታ** |  |  | 1 |

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው የኖታ ስሞች ፣ የኖታ ምልክቶች ፣ የእረፍት ምልክቶች እና የጊዜ ቆይታን ያመለክቱናል፡፡

**መልመጃ** 1.2

1. ተማሪዎች ከ ሙሉ ኖታ እና ሙሉ እረፍት እስከ ሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ እንዲሁም የጊዜ ቆይታቸውን በመፃፍ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡
2. ከታች የተቀመጡ የኖታና የረፍት ምልክቶችን በማንበብ ተለማመዱ



**ፍንጭ**

1. ተማሪዎች የኖታ ምልክቶችንና የእረፍት ምልክቶችን ሲፅፉ በትክክል መፃፋቸውን እና የጊዜ ቆይታቸውን በትክክል ማስቀመጣቸውን ያረጋግጡ፡፡
2. መምህር በተማሪዎች የመማሪያ መጽሃፍ ላይ የተቀመጡ የተቀመጡ የኖታና የረፍት ምልክቶችን በማንበብ እንዲለማመዱ ያድርጉ

## 1.2. ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች ስለ ዝርግ ቅርፆች ባህሪያት እና አይነቶች ይማራሉ። መምህሩም ተማሪዎችን ስለ ዝርግ ቅርፆች ባህሪያት በዝርዝር ያስረዳሉ። ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ የሆኑ ዝርግ ቅርፆችን ከአካባቢያቸው ጋር በማዛመድ ለይተው እንዲያውቁ ያደርጋሉ:።

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ከዚህ ርዕስ በኋላ ተማሪዎች ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን ለይተው ያውቃሉ
- ተማሪዎች ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ያጠናሉ ለይተውም ያውቃሉ
- ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርፆችን ለይተው ያውቃሉ

በአካባቢያቸው የሚገኙ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ነገሮችን ይዘረዝራሉ

### ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- በቻርት ወይም በልሙጥ ወረቀት በተለያዩ ቀለማት የተሰሩ ዝርግ ቅርፆች
- ቀለሞች
- ባለ ቀለም እርሳስ ወይም ማርከር
- ባለ ቀለም ቾክ/ክራዮን
- ልሙጥ ወረቀት

### የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ዝርግ ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት እንዲስሉ ያደርጋሉ
- የሳሉት ዝርግ ቅርጽ ላይ ቀለም በትክክል እንዲቀቡ ይከታተላሉ

- ዝርግ ቅርፆች ላይ ቀልም በመቀባት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ እገዛ ያደርጋሉ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን ሰርቶ በማሳየት
- ተማሪዎች መምህሩ ሲስል ተማሪዎች በትክክል እንዲመለከቱ ማድረግ
- መምህሩ ተማሪዎችን ስላስተማራቸው ነገሮች መልሶ በመጠየቅ እንዴት እንደተረዱት በማወቅ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ አይነት ቅርጽ እና ቀለም ያላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ፡፡


**መልስ**

- አራት ማዕዘን ወረቀቶች ፣ ነጭ ቾክ ፣ ጥቁር ሰሌዳ ፣ ቀይ እስክርቢቶ ፣ ሰማያዊ መጽሃፍ …ወዘተ

**ጠቃሚ መረጃ**

ዝርግ ቅርፅ የሚፈጠረው አንድ መስመር ከተነሳበት ነጥብ ዞሮ ሲገጥም ነው፡፡ ዝርግ ቅርጽ (two dimensional shape) በቁመትና በርዝመት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው ስንል ጥልቀት የሌለው መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ እነዚህም ነገሮች ግድግዳ ላይ ፣ ወረቀት ላይ ፣ መሬት ላይ ወይም በማንኛውም ጠፍጣፋ መደብ ላይ ተስለው ልናገኛቸው እንችላለን፡፡ የተለያዩ አይነት ዝርግ ቅርፆችን እናገኛለን፡፡ እነርሱም መደበኛ ፣ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ዝርግ ቅርፆች ናቸው፡፡ ለምሳሌ

መደበኛ የምንላቸው ክብ ፣ ሶስት ማእዘን ፣ ሬክታንግል ፣ ትራፒዝየም እና ፓራሌሎግራምን መጥቀስ እንችላለን:: ተፈጥሯዊ የምንላቸው ደግሞ በተፈጥሮ የተገኙ ሲሆኑ ሰማይ ላይ ያለ የዳመና ቅርፅ ፣ የዛፎች ውጫዊ ቅርፆች ፣ እንዲሁም የተለያዩ ድንጋዮች ውጫዊ ቅርፆች ናቸው::



ምስል 1.2- ሰው ሰራሽ ዝርግ ቅርፆች (geometric shepes)



ምስል 1.3- ተፈጥሯዊ ዝርግ ቅርፆች (organic shapes)

ዝርግ ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት መለማመድ ለልጆች የመሳል ፣ የማስታወስ እንዲሁም የማገናዘብ ችሎታን ይጨምራል፡፡ የተለያዩ ባለ ሁለት አውታረ-መጠን ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት መቀባት እና ማጥናት ስንል ንድፎችን በመሳል ቀለም መቀባትን እንዲረዱ ማድረግ መቻልን ነው፡፡ በመጀመሪያ ዝርግ ቅርፆችን መምህሩ ሲስል ያያሉ ፣ ቀጥሎ የመስመሮችን እንቅስቃሴ ጠብቀው እንዴት ቀለም መቀባት እንደሚችሉ ይገነዘባሉ፡፡ ዝርግ ቅርፆችን ቀለም ሲቀቡ ጥንቃቄን እና ውበትን በማሰብ ወጥ የሆኑ ቀለማትን በእኩል መጠን መቀባት እንዲለመለማመዱ ለማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**መልመጃ 1.3**

መምህር ተማሪዎች የኢትዮጵያን ካርታ ስለው የተለያዩ ክልሎችን በተለያየ ቀለም እየቀቡ ስለዝርግ ቅርፆች ለተማሪዎች ያሳዩ፡፡

## 1.2.2. ዝርግ ቅርፆችን በተለያዩ ቀለማት ማጥናት

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- እርሳስ
- እስክርቢቶ
- ቀለም
- ብሩሽ
- ወፍራም ወረቀት
- ፓርከር/ክራዩን
- ባለቀለም ቾክ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- በክፍላቸው ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ምን አይነት ቀለማት እንዳላቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

**መልስ**

- ጥቁር ሰሌዳ ጥቁር ቀለም ፣ ቾክ ነጭ ቀለም ፣ ወረቀት ነጭ ፣ ቀይ እስክርቢቶ ፣ አረንጓዴ መጽሃፍ.... ወዘተ

**ጠቃሚ መረጃ**

በዚህ ንኡስ ርዕስ መምህሩ ተማሪዎችን ዝርግ ቅርፆችን እንዴት ቀለም መቀባት እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡ የዝርግ ቅርፆችን ባህሪ ከመረዳት በተጨማሪ ቅርፆችችን

ተማሪዎች  እንዲያውቁ ያግዛቸዋል፡፡ ስለዚህ መምህሩ ለተማሪዎች የተለያዩ ቀለማቶችን በመቀባት ያሳያሉ፡፡  ቅርፅ ስንል ከቁመትና ርዝመት በተጨማሪ ይዘት ወይም ጥልቀት ያለው መሆኑን እንዲሁም ራሳቸውን ችለው መቀመጥ የሚችሉና ከተለያዩ አቅጣጫዎች ልንመለከታቸው የምንችላቸው ሲሆኑ ነው፡፡ አንድን ቅርፅ ከፊት ለፊት ፣ ከጎን እንዲሁም ከላይ ሆነን ልንመለከተው እንችላለን፡፡ በመሰረታዊነት የዝርግ ቅርፅ እና ቅርፅ ልዩነት የይዘት/ጥልቀት መኖር እና አለመኖር ይሆናል፡፡ ልክ እንደ ዝርግ ቅርፅ ቅርፅም ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርፅ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ለምሳሌ ሳጥን ፣ ሲሊንደር ፣ ኮን ፣ ፒራሚድ እንዲሁም ሉልን ልንጠቅስ እንችላለን፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን ምሳሌዎች አይነት በየቤታችን ብዙ ቁሳቁሶችን ማግኘት እንችላለን፡፡ ብርጭቆ ፣ ኳስ ፣ የቡና ሲኒ ፣ ቁም ሳጥን … ወዘተ ቅርፆች በየቤታችን ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ተፈጥሯዊ ቅርፆችን በተመለከተ እንዲህ ነው ብለን ልንናገር ወይም ስም ልንሰጣቸው አንችልም፡፡

ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆችን ተማሪዎች ቀለም ሲቀቡ በዋናነት የተለያዩ ቀለማትን እንዴት በአንድ ስዕል ውስጥ መጠቀም እንደሚችሉ ለማለማመድ ነው፡፡ መምህሩ ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆችን ቀለም ሲቀቡ በተወሰነ መጠን ስለ ጥላ እና ብርሃን ወይም ከላይና ከታች ያለውን የስዕሉን ክፍል ለመለየት ከአንድ በላይ ቀለማትን ተጠቅመው በመቀባት ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ አንድን ሳጥን ነድፈው ከጨረሱ በኋላ የሳጥኑን ሶስት ጎኖች በተለያዩ ቀለማት ቀብተው ቢያሳዩ ተማሪዎች የተሻለ የመረዳት እድል ያገኛሉ፡፡

**መልመጃ 1.4**

- መምህሩ ተማሪዎችን በየቤታቸው የሚገኙ መደበኛ ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆችን እና ኢ-መደበኛ ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆችን እንዲዘረዝሩና ወረቀት ላይ በእርሳስ ወይም ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመሳል እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡

**መልስ**

- መምህሩ ተማሪዎችን የተለያዩ ቀለማትን ቅርፆች ላይ እየቀቡ እንዲለማመዱ መንገዶችን ያሳዩ፡፡

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎች በማየት እንዲረዱ ማድረግ
- የተረዱትን በቃል መጠየቅ

## 1.3. ምጥን ተውኔቶችን መረዳት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች የተለያዩ ምጥን ተውኔቶችን የረዳሉ፡፡ ምጥን ተውኔት በትውን ጥበብ ውስጥ የሚመደብ የተውኔት አይነት ነው፡፡ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ለመኖር ሲል የተለያዩ ክንዋኔዎችን ይተውናሉ፡፡ በዚህም መሠረት የተለያዩ የተፃፉ ወይም ያልተፃፉ ክንውኖችን እጥር ምጥን ያሉ ታሪኮችን በመምረጥ ለእይታ እንዲቀርቡ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የተውኔት አሰራር መንገድ ምጥን ተውኔት ይባላል፡፡ ምጥን ተውኔት አጭር ግልፅ በሁሉም መንገድ የተመጠነ ሲሆን እንደ ተውኔቱ አይነት ፅሑፈ-ተውኔት (ድርሰት) ሊኖረውም ሆነ ላይኖረውም ይችላል፡፡ ምጥን ተውኔት ከድንገቴ ፈጠራ ተውኔት ጋር ይቀራረባል ወይም ይወራረሳል፡፡

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- ስለ ድምፅ-አልባ ተውኔት ምንነት በሚገባ ይረዳሉ
- የድምፅ-አልባ ተውኔት መሰረታዊ ነገሮችን ይረዳሉ
- ድምፅ-አልባ በሆነ መንገድ መሰራት የሚችሉ ነገሮችን በሚገባ ይለያሉ
- አንድን ሃሳብ ስሜትን ብቻ በመጠቀም ይገልፃሉ

### ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- መምህሩ ድምፅ-አልባ ተውኔት ለመስራት የሚያስፈልጉትን አልባሳት ተማሪዎችን እንዲያመጡ ያደርጋል

- የተቀረጹ ድምፅ-አልባ ተውኔቶች እና ተንቀሳቃሽ ምስሎች ካሉ ለተማሪዎች ያሳያሉ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ስለ ድምጽ አልባ ተውኔቶች በቂ ማብራሪያ ይሰጣሉ
- ስለ ድምጽ አልባ ተውኔቶች በምሳሌና በድርጊት ያሳያሉ
- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቀላል ድምጽ አልባ ተውኔቶችን እንዲያሳዩ ያደርጋሉ

**የግምገማ እና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎችን የተመለከቱትን ነገር እንዲያብራሩ ማድረግ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ➢ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለተመለከታችሁት አጭር ድራማ ወይም ተውኔት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ

**ፍንጭ**

- ➢ መምህሩ ተማሪዎችን ከዚህ በፊት ስለተመለከቷቸው አጭር ድራማዎች በመጠየቅ ለእለቱ ክፍለ ጊዜ እንደ መነሻ ሃሳብ ይጠቀሙበት

**መልመጃ 1.5**

- ከሁለት እስከ አምስት ገጽ ያላቸውን ተውኔቶች በመምረጥ በክፍል ውስጥ ሰርታችሁ ለጓደኞቻችሁ አሳዩ

**ፍንጭ**

- *መምህሩ ተማሪዎችን መጥን ተውኔቶችን ጽፈው እንዲለማመዱ ያመቻቹ*

## 1.4. የቁምና አግዳሚ ፎቶግራፍ አነሳስ አይነቶችን መረዳት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

**መግቢያ**

ፎቶ ግራፍ የአንድን ሰው ፣ እንስሳ ወይም የተፈጥሮ መልክዓ-ምድር ወደ ምስል በመቀየር ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ነው:: ፎቶ አንድን ቅጽበታዊ ነገር ባለበት እንድናስታውሰው የሚያደረግ ፈጠራ ነው:: የድሮ ፎቶዎች በጥቁር እና ነጭ ቀለማት ብቻ የሚነሱ ሲሆን የአሁን ጊዜ ፎቶዎች ደግሞ ብዙ ቀለማት ያላቸው ናቸው:: መምህሩ ይህን ለማስረዳት የተለያዩ አይነት ፎቶዎችን በምሳሌነት በማሳየት ተማሪዎች እንዲረዱት ማድረግ ይችላሉ::

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ከጨረሱ በኋላ የተለያዩ አይነት የፎቶ አነሳስ አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ
- መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያንን ይረዳሉ

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- የተለያዩ አይነት ፎቶግራፎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ስለ ፎቶግራፍ በቂ ማብራሪያ መስጠት
- የቁምና አግዳሚ የፎቶግራፍ አይነቶችን በቂ ማብራሪያ መስጠት
- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚመለከቷቸው ፎቶግራፎች እንዲናገሩ ማድረግ
- ጥያቄ በመጠየቅ ምን ያህል እንደተረዱ ማራጋገጥ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- በመመልከት
- በገለፃ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት ፎቶ ተነስተው የሚያውቁ መሆኑን ፣ መቼ እና የት ፎቶ እንደተነሱ በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ይህንን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ስለ ፎቶግራፍ ያላችውን ቅድመ ግንዛቤ ከመረዳት በተጨማሪ ፎቶ የተነሱባቸውን አጋጣሚዎች እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ስለ ፎቶግራፍ አነሳስና አይነቶች ከማንሳታችን በፊት ተማሪዎች ስለ ፎቶግራፍ ማንሻ ካሜራ መቼ እና እንዴት እንደ ተጀመረ ማስተማር ይገባናል፡፡ ምክንያቱም ከፎቶግራፍ ታሪክ በፊት የካሜራ መገኘት ስለሚቀድም ነው፡፡ በአለም ላይ የመጀመሪያው ካሜራ የተፈጠረው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1816 በኒስፎሪ ኒፕሲ አማካኝነት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በፎቶግራፍ ታሪክ ረጅም ዘመን

ያስቆጠረው ፎቶግራፍ የተነሳው በኒስፎሪ ኒፕሲ አማካኝነት የተነሳው ፎቶ እንደሆነ ይታመናል። በዚህም እስካሁን ባለው መረጃ መሠረት ረጅም ዘመን ያስቆጠረው ፎቶግራፍ እንደሆነ የተለያዩ መዛግብት ላይ ተፅፎ ይገኛል። የመጀመሪያው ካሜራ የሳጥን ቅርጽ የነበረው ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን እጅግ ብዙ አይነት ካሜራዎች በተለያየ መጠን እና ቅርጽ ተሻሽለው ይገኛሉ። በዋናነት የካሜራ ጥቅም ምስሎችን በፎቶግራፍና በተንቀሳቃሽ ምስል መልክ ማስቀረት እና ወደ ወረቀት በህትመት መልክ መቀየር ነው።

በኢትዮጵያም ለመጀመሪያ ጊዜ የፎቶግራፍ ማንሻ ካሜራ ወደ ሃገራችን የገባው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በ1875 ዓ.ም እንደሆነ የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ፎቶ የተነሳው ግንቦት 13 ቀን 1875 ዓ.ም አጼ ምኒልክ ነው። ከዚያ በኋላ የቤተ-መንግስት ፎቶ ግራፍ አንሺ የነበረው ቦያጂያን በ1897 ዓ.ም የመጀመሪያውን የህዝብ ፎቶ ቤት በአዲስ አበባ በመክፈት ፎቶን ለህዝብ አስተዋውቋል።

### 1.4.1. መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያን

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- የተለየዩ ፎቶዎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያንን በሚገባ ያስረዳሉ
- ከዚህ በፊት ተማሪዎች የተመለከቷቸውን ፎቶዎች ከሚማሩት ትምህርት ጋር እንዲያገናኙት ያደርጋሉ
- በመጨረሻ ተማሪዎች ምን እንደተረዱ ለማረጋገጥ ጥያቄ ይጠይቃሉ

## የግምገማ እና ክትትል ስልት

- በጥያቄ እና መልስ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ፎቶ ግራፍ የሚያነሳ ሰው ምን አይነት እንቅስቃሴዎችን እንደሚያሳይ ተማሪዎች እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

**ፍንጭ**

- በዚህ ርዕስ ተማሪዎች እንዲያነሱት የሚፈለገው አንድ ፎቶ አንሺ ፎቶ ከማንሳቱ በፊት የሰዎችን አቋቋም ፣ የብርሃን ሁኔታ ፣ ሰዎች ፈገግ እንዲሉ ወይም የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማስተካከል ፎቶው እንዲያምር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንዲገልጹ ማድረግ ነው፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

በመጀመሪያ ደረጃ ካሜራ ይዘን ፎቶግራፍ ከማንሳታችን ወይም ለተማሪዎች ከማስተማራችን በፊት ለማንሳት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነጥቦችን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የፎቶግራፍ መሰረታዊ ነገሮች የምንላቸው ብዙ ቢሆኑም በዋናነት ግን ብርሃን ፣ ቀለም ፣ እንቅስቃሴ እና ንድፈ-ሃሳብ መሰረታዊ ነገሮች ናቸው፡፡ ብዙ አይነት የፎቶ ግራፍ አነሳስ አይነቶች ቢኖሩም በዋናነት ግን የቁም (portrait) እና አግዳሚ (landscape) ተብለው ይከፈላሉ፡፡

**መልመጃ 1.6**

ተማሪዎች ከታች በምስሉ ላይ የሚያዩትን ፎቶግራፍ በመመልከት ስለ ጥላ እና ብርሃን እንዲናገሩ ያድርጓቸው



ምስል 1.4- የአፕል ፎቶግራፍ

**መልስ**

- የብርሃን አቅጣጫ ከቀኝ ወደ ግራ በአፕል ፍሬው ላይ አርፏል። ከብርሃን አቅጣጫ በተቃራኒ ጥላ ይፈጠራል ማለት ነው።

**መልመጃ 1.7**

- ተማሪዎች ከታች በምስሉ ላይ በሚታየው ፎቶግራፍ ውስጥ የሚመለከቷቸውን ቀለሞች እንዲናገሩ ያድርጓቸው።



ምስል 1.5- የምሽት ፎቶግራፍ

**መልስ**

- ከላይ በምስሉ ላይ የሚታየው ፎቶግራፍ ላይ ብዙ የቀለም አይነቶች ይታያሉ። ለምሳሌ ደማቅ ሰማያዊ ፣ ደብዛዛ ሰማያዊ ፣ ብርቱካናማ ፣ ነጭ፣ እንዲሁም ጥቁር ቀለማትን ማየት እንችላለን። በአንድ የምሽት ፎቶግራፍ ላይ የሚታዩ ቀለማት በእኩለ ቀን ሰዓት ላይ ላንመለከታቸው እንችላለን። ስለሆነም የፎቶዎቹ ቀለማት ከሰዓቱ ብርሃን ጋር የተያያዙ ናቸው።

## መልመጃ 1.8

- ከታች በምስሉ ላይ የምመለከቱት አትሌት ሀይሌ ገብረ ስላሴ በምን አይነት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳለ ምስሉን አይተው እንዲናገሩ ያድርጓቸው።




ምስል 1.6 - ሀይሌ ገብረ ሥላሴ

**መልመጃ 1.9**

**መምህር ከታች በምስሉ ላይ የሚመለከቱትን ፎቶግራፍ አወቃቀር እና አቀማመጥ እንዲገልጹ ያድርጓቸው**



ምስል 1.7- አወቃቀርን የሚያሳይ ፎቶግራፍ

**መልስ**

- በዚህ ምስል ውስጥ ስለ ፎቶግራፍ አወቃቀር በደንብ መናገር እንችላለን፡፡ ለምሳሌ የአራቱም ቅርፆች ቁመት የተለያየ መሆኑ፣ የእቃዎች ቅርጽ እና ስፋት የተለያየ መሆኑ እና አቀማመጣቸው ለፎቶግራፉ ትልቅ ውበትን ፈጥሮለታል ማለት ነው፡፡

**መልመጃ 1.10**

- ተማሪዎች በተለያዩ መማሪያ መጽሕሐፍት ውስጥ ያሉትን ፎቶግራፎች የቁም ወይም አግዳሚ የፎቶ አነሳስ አይነቶች መሆናቸውን በቡድን ሆነው በመለየት እንዲወያዩባቸው ያድርጉ

**ፍንጭ**

- ከላይ ያለውን ጥያቄ መሰረት በማደርግ በተለያዩ መማሪያ መጽሐፍት (የታሪክ ፣ የማህበራዊ ሳይንስ እና የተፈጥሮ ሳይንስ መጽሃፍት) ውስጥ ያሉትን ፎቶግራፎች የቁም ወይም አግዳሚ የፎቶ ግራፍ አይነቶችን እንዲለዩ ያድርጉ

### 1.4.3. ፎቶዎችን በመመልከት መልዕክቶችን መረዳት

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- የተለያዩ አይነት ታሩካዊና ባህላዊ ነገሮችን የያዙ ፎቶግራፎች

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- መምህሩ የተለያዩ ፎቶዎችን በማሳየት እንዲያብራሩ ማድረግ
- ሌሎች በቤታቸው ውስጥ የሚገኙ ፎቶዎችን ይዘው እንዲመጡ በማድረግ ውይይት መፍጠር

**የማነቃቂያ ተግባር**

- እስካሁን ካያችኋቸው የፎቶ አይነቶች የወደዳችሁትን ፎቶ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ፡፡

**ፍንጭ**

- ይህ ጥያቄ መምህሩ ተማሪዎችን ስለተመለከቷቸው የፎቶ ይዘቶች እንዲናገሩ መገፋፋት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ መምህሩ ከተማሪዎች የሚያገኘውን ግብረ መልስ በመጠቀም ለመሸጋገሪያነት ይጠቀመዋል ማለት ነው፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ከሺህ ቃል አንድ ስዕል እንዲሉ በአንድ ፎቶ ውስጥ ከሺህ በላይ ቃላትን መግለፅ እንችላለን፡፡ ፎቶዎች የአንድን ማህበረሰብ ባህል ፣ ሃይማኖት ፣ የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የዕለት ከዕለት የኑሮ ሁኔታን ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ አንድ ፎቶ በውስጡ አንድና ከዚያ በላይ መልዕክቶችን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ በአንድ ፎቶ ውስጥ ከሺህ በላይ ቃላትን መግለፅ እንችላለን፡፡ ፎቶዎች የአንድን ማህበረሰብ ባህል ፣ ሃይማኖት ፣ የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የዕለት ከዕለት የኑሮ ሁኔታን ሊገልፅ ይችላል፡፡ አንድ ፎቶ በውስጡ አንድና ከዚያ በላይ መልዕክቶችን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በጉራጌ ዞን የሚገኘውን የጥያ ትክል ድንጋይ ብንመለከት ከብዙ አመታት በፊት በዚያ ቦታ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን ታሪክ ፣ ባህል ፣ ስልጣኔ እና ሌሎችንም ነገሮች ይገልፃል፡፡ የአንዲት የሀመርን ሴት ፎቶ በመመልከት ምን አይነት ባህል ፣ አኗኗር እና ስልጣኔ ደረጃ ላይ እንደደረሰች በጥቂቱም ቢሆን መናገር እንችላለን፡፡ የወላይታን የጊፋታ በዓል ፣ የጉራጌን መስቀል ፣ የጋሞን

ባህላዊ የእርቅ ስርዓት ፣ የኮንሶን የእርከን ስራ… ወዘተ ፎቶግራፎችን በመጠቀም ማሳየት እንችላለን ወይም ከፎቶዎች አይተን መረዳት እንችላለን፡፡

ተማሪዎች አንድን ፎቶ በመመልከት ፅሁፍ ያዘጋጃሉ ፣ ታሪክንና ባህልን ወክለው ትረካዎችን ያዘጋጃሉ ያስረዳሉ ፣ ለውይይት እና ለክርክር የሚሆኑ ሃሳቦችን እንዲነሱ ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ የጋሞ አባቶች ግጭት ሲፈጠር እንዴት በባህላዊ መንገድ እንደሚያስቆሙት በፎቶ አስደግፈን ብናቀርብና ከፎቶው ተነስተው ተማሪዎች ሙዚቃዊ ፣ ስዕላዊ እንዲሁም ድራማዊ በሆነ መንገድ እንዲያሳዩ ማድረግ ተማሪዎች በአንድ ፎቶ ብዙ ነገር እንዲማሩ ያግዛቸዋል፡፡

**መልመጃ 1.11**

- ተማሪዎች የተለያዩ ፎቶዎችን ከጋዜጣ ላይ በመሰብሰብ ስለ ይዘታቸው ማብራሪያ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህር ተማሪዎች ያመጧቸውን ፎቶዎች በማወዳደር የተሻሉ ፎቶግራፎች የሰበሰበውን ቡድን በማበረታታት ውጤት ይስጡ፡፡




ምስል 1.8- የጋሞ አባቶች ግጭትን ለማስቆም እርጥብ ሳር በእጃቸው ይዘው የሚያሳይ ፎቶ

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ በአካባቢያችን የሚገኙ የተለያዩ ነገሮችን እንዴት መመልከት እንደምንችል አይተናል፡፡ ምልከታ አንድን ነገር ከመስራታችን በፊት ማድረግ ያለብን የሁል ጊዜ ተግባር ነው፡፡ ለዚህም የትውን እና እይታ ጥበባትን ከአካባቢያችን ጋር በማዛመድ የተለያዩ አይነት ጽሁፎችን ፣ ስዕሎችን ፣ መዝሙሮችን እንዲሁም ተውኔቶችን ለመስራት ያግዘናል፡፡ አካባቢያችንን መመልከት ስንጀምር የተፈጥሮን ውበት ማለትም የዛፎችን እንቅስቃሴ ፣ የእንስሳትን ድምጽ ፣ የፏፏቴዎችን ድምጽ ፣ የአበቦችን ቀለማት ለማየትና ለማስመሰል ያግዘናል፡፡ በአጠቃላይ አካባቢያችንን መመልከት ስንጀምር የተለያዩ አይነት ፈጠራዎችን እና ችግር ፈቺ ምርምሮችን በትምህርት ቤታችንም ሆነ በመኖሪያ መንደራችን መስራት እንችላለን ማለት ነው፡፡

### የማጠቃለያ መልመጃ

1. ድምጽ አልባ ተውኔት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይግለጹ
2. ተማሪዎች የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን ፎቶዎች ሰበብስበው በማምጣት በክፍል ውስጥ ውድድር ያድርጉ
3. ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ በቀላል ስልተ-ምቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን በመለማመድ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ
4. የኖታ እና የእረፍት ምልክቶችን የጊዜ ቆይታ ለማወቅ ተማሪዎች በእግራቸው መሬቱን በመምታት ወይም በእጃቸው በማጨብጨብ እየቆጠሩ ይለማመዱ
5. ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቁትን ሰው በማስመሰል በድምፅ-አልባ ተውኔት እንዴት እንደሚገልፁት ለጓደኞቻቸው ያሳዩ
6. ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን ተማሪዎች በቤታቸው ውስጥ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ጋር ያመሳስሉ

**መልስ**

1. ድምጽ አልባ ተውኔት ማለት ያለ ንግግር ወይም ያለ ድምጽ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ብቻ በመጠቀም የምናሳየው ተውኔት ነው።
2. በዚህ ጥያቄ መምህሩ ተማሪዎችን የተለያዩ ፎቶዎችን እንዲያመጡ በማድረግና ውድድር በማካሄድ የመነቃቃት ስሜት እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል
3. በእጅ እና በእግራቸው የተለያዩ ቀላል ስልተ ምቶችን እንዲዘምሩ ማድረግ
4. የድምጽ እና የእረፍት ምልክቶችን በመቁጠር ድምፆችን እንዲለዩ ማድረግ
5. በአካባቢያቸው ወይም በሰፈራቸው የሚያውቁትን ሰው እንቅስቃሴ በድምጽ አልባ ተውኔት እንዲያሳዩ መምህሩ እገዛ ያደርግላቸዋል።
6. በቤታቸው ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ማለትም ምጣድን ፣ ባልዲን ፣ ድስትን ፣ ብርጭቆን እንዲሁም ሌሎችን ቁሳቁሶች ከተለያዩ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ቅርፆች ጋር እያዛመዱ እንዲያውቁ ያደርጋል።

| ምዕራፍ ሁለት | 2. የግልና የቡድን ትግበራዎች<br><br>ለምዕራፉ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 28 |
|---|---|

**መግቢያ**

በምዕራፍ ሁለት መምህሩ የተለያዩ አይነት የሙዚቃ ምልክቶችን ማለትም ስታፍን እና ክሌፍን እንዲያውቁና እንዲረዱ ያደርጋል። የተለያዩ የኮላጅ ስዕሎችን አካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመለጣጠፍ ፣ በመገጣጠም ወይም በመቆራረጥ ልምምድ እንዲያደርጉ እና አስፈላጊ ሲሆንም ሰርተው እንዲያሳዩ ያደርጋል። ተማሪዎች ሀገረሰባዊ ውዝዋዜዎችን እና መዝሙሮችን በግልም ሆነ በቡድን ሆነው እንዲዘምሩና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ ልዩ ፕሮግራም ላይ እንዲያቀርቡ ያደርጋል። ሃገረሰባዊ ዜማዎችን ሲለማመዱ ተማሪዎች አካባቢያቸውን ባህላቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ያግዛቸዋል። መምህሩም ተማሪዎቹ በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ያግዛቸዋል። ድምፅ-አልባ ተውኔቶችን እና ግለ-ተውኔቶችን በግልም ሆነ በቡድን እንዲለማመዱ እና በተማሪዎች ፊት እንዲያቀርቡ እድሉን እንዲያመቻች ከመምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው።

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የተለያዩ የሙዚቃ ምልክቶችን (staff & clef) እና ረዳት መስመሮችን ለይተው በማወቅ ይዘምራሉ
- የኮላጅ ስዕሎችን በአካባቢያቸው በሚገኙ ቁሳቁሶች ይሰራሉ
- ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎችን እና ውዝዋዜዎችን ይለማመዳሉ
- ግለ-ተውኔቶችን ተለማምደው ለተማሪዎች ያቀርባሉ

### የመማር ማስተማር ግብዓቶች

- የመለማመጃ አዳራሽ/ክፍል
- ለኮላጅ መስሪያ የሚያገለግሉ የወዳደቁ ቁሳቁሶች
- ኮላ/ሙጫ
- ከበሮ፣ ጥሩምባ፣ ፊላ
- መቀስ
- ማስመሪያ
- ለግለ-ተውኔት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቀለሞች

### የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ተማሪዎችን በስታፍ ላይ መፃፍ እንዲለማመዱ ያደርጋሉ
- በአካባቢያቸው የወዳደቁ ነገሮችን በመጠቀም የኮላጅ ሥዕል እንዲሰሩ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ሀገረሰባዊ ውዝዋዜዎችን ተለማምደው እንዲያቀርቡ መድረክ ያመቻቻሉ
- ግጥም እና ግለ-ተውኔት ተማሪዎች እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣሉ

### የግምገማና ክትትል ስልት

- በተግባር ሲሰሩ በማየት
- ተውኔቶችን መድረክ ላይ ሲያሳዩ በማየት

## 2.1. የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (ስታፍ) እና ቁልፎች (ክሌፍ)

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 7

**መግቢያ**

የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ የሚባለው አምስት መስመር ያለው እና አራት ክፍት ቦታዎች ያሉት ሲሆን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳውን በመሳል እና ቁልፎችን በማስቀመጥ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳን እንገልፃለን፡፡ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ በዉስጡ በርካታ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም በዚህ የ4ኛ ክፍል ደረጃ የምናየው የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መስመሮች እና ክፍት ቦታዎችን መሳል እና ማብራራትን እና በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ቁልፎችን ማስቀመጥ/መሳል/ እንዲሁም ኖታዎች የሚቀመጡበትን ቦታዎች መለየት ይሆናል፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ሲያጠናቅቁ

- የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ እና ቁልፎችን ለይተው ያውቃሉ
- በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ ያሉ ረዳት መስመሮችን ያውቃሉ
- በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ ያሉትን ቁልፎች በማየት መዝሙር ይዘምራሉ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳን በመሳል ያሳያሉ
- በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ የሙዚቃ ቁልፎች እንዴት እንደሚሳሉ ያስረዳሉ
- በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ የተሳሉ ቁልፎችን በማየት በጋራ ይዘምራሉ

## የግምገማ እና ክትትል ስልቶች

- ተማሪዎች የሚስሏቸውን የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳን እና በሳሉት የሙዚቃ መፃፊያ ላይ በቦታቸው የሚያስቀምጧቸውን ቁልፎችና ኖታዎች በመመልከት ውጤት ይሰጣሉ


| |
|---|
| **ማነቃቂያ**<br>➢ ሙዚቃን በሙዚቃ መሳርያ የሚጫወቱ ሰዎች እንዴት እንደሚጫወቱ ተማሪዎች ያላቸውን ግንዛቤ ይጠይቋቸው፡፡<br>**ፍንጭ**<br>➢ በወረቀት ላይ የተፃፈ የሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ ቁልፎችንና የሙዚቃዉን ኖታዎች በመምልከት በተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ **(ይሄ በልምድ የሙዚቃ መሳርያ የሚጫወቱ ሙዚቀኞችን አይመለከትም)**፡፡ |

**ጠቃሚ መረጃ**

የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ (staff) የምንለው አምስት መስመር ያለው እና አራት ክፍት ቦታዎች ያሉት ሲሆን ተማሪዎች የሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳውን በመሳል እና ቁልፎችን በማስቀመጥ የሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳን እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡

የሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳ በዉስጡ በርካታ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም በዚህ የ4ኛ ክፍል ደረጃ መማር ያለባቸው የሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳ መስመሮች እና ክፍት ቦታዎችን መሳል እና ማብራራት አንዱ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳ ላይ ቁልፎችን ማስቀመጥ/መሳል/ እና ኖታዎች የሚቀመጡበትን ቦታ እንዲለዩ ማድረግ ይሆናል፡፡


እነዚህን የመሰመር ቦታዎች እና የክፍት ቦታዎች የምንቆጥራቸው ከታች ወደ ላይ እንደሆነ ለተማሪዎች ያስረዱ፡፡




ምስል 2.1-በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የመስመር ቦታዎችና ክፍት ቦታዎች ቅደም-ተከተል


**የሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳ ላይ ቁልፎችን ማስቀመጥ (መሳል)**

ከታች በምስል 2.2 እንደምንመለከተው በሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳ ላይ ያለው የቁልፍ ምልክት G ቁልፍ ወይም (treble cleff) ብለን የምንጠራው ሲሆን የሙዚቃ መፃፍያ ሠሌዳ መስመር ላይ ያሉ የኖታ ስሞች ሲሆኑ ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ E (ሚ), G (ሶል), B (ሲ) D (ሬ) F (ፋ) እንደሆኑ ለተማሪዎች ያስረዳሉ





ምስል 2.2 G ቁልፍ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መስመሮች ላይ የሚቀመጡ ኖታዎች

በምስል 2.3 ያለው የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ክፍት ቦታዎች ላይ ያሉ የኖታ ስሞች ሲሆን ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ F (ፋ) A (ላ) C (ዶ) E (ሚ) እንደሆኑ ለተማሪዎች በሚረዱት መንገድ ያብራራሉ ።




ምስል 2.3 G ቁልፍ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ክፍት ቦታዎች ላይ
የሚቀመጡ ኖታዎች


በምስል 2.4 የምንመለከተው በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ያለው የቁልፍ ምልክት F ቁልፍ (Base claf) ብለን የምንጠራው ሲሆን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መስመር ላይ ያሉ የኖታ ስሞች ሲሆኑ ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ G (ሶል) B (ሲ) D (ሬ) F(ፋ) A (ላ) እንደሆኑ ለተማሪዎች ያብራራሉ።




ምስል 2.4 F ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መስመሮች ላይ
የሚቀመጡ ኖታዎች

በምስል 2.5 ላይ የተጠቀሰው በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ያለው የቁልፍ ምልክት F ቁልፍ (bass clef) ብለን የምንጠራው ሲሆን የሙዚቃ መፃፊያ

ሠሌዳ መስመር ላይ ያሉ የኖታ ስሞች ሲሆኑ ከታች ወደ ላይ ሲነበቡ A (ላ) C (ዶ) E (ሚ) G (ሶል) እንደሆኑ ለተማሪዎች አስረዷቸው።





ምስል 2.5 F ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ክፍት ቦታዎች ላይ የሚቀመጡ ኖታዎች

- **መልመጃ** 2.1
- እባክዎት መምህር የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳን በመሳል ፣ ቁልፎችን በማስቀመጥ እና የኖታዎችን ቦታ በመለየት ለተማሪዎቹ አሳዩ።

**ለ. የሙዚቃ ቁልፎች (Clef)**


ከሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የምንስላቸው አራት አይነት የሙዚቃ ቁልፎች (cleff) አሉ። ነገር ግን በዚህ የአራተኛ ክፍል ደረጃ የምንማረው ስለ ሁለት ቁልፎች (cleff) ይሆናል። እነሱም G-ቁልፍ እና F-ቁልፍ ናቸው።

**G ቁልፍ (treble clef)** የምንለው አምስት መስመር እና አራት ክፍት ቦታ ያለውን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ከሳልን በኋላ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መነሻውን ቆጥረን ከሁለተኛው መስመር ላይ መነሻ አድርገን እንስለዋለን። ከመነሻው ተነስተን ስንስለው G ፊደልን ስለሚመስለው G ቁልፍ የሚል ስያሜ ተሰጠው።



ምስል 2.6- የG ቁልፍ አፃፃፍ ስልት

F ቁልፍ (bass cleff) የምንለው አምስት መስመር እና አራት ክፍት ቦታ ያለውን የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ከሳልን በኋላ የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ መነሻውን ቆጥረን ከአራተኛው መስመር ላይ መነሻ አድርገን እንስለዋለን



ምስል 2.7. የ F ቁልፍ አፃፃፍ ስልት

## ሐ. የረዳት መስመር

የረዳት መስመር ማለት፡- የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የሙዚቃ ኖታዎችን በምንፅፍበት ወቅት ከሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ ከላይ እና ከታች ተርፈው የሚወጡ የሙዚቃ ኖታዎችን የምንፅፈው በረዳት መስመሮች ላይ ይሆናል።


ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች የምንመለከተው በ G ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የረዳት መስመሮችን ቦታ ይሆናል።



ምስል 2.8 ኖታ ያልተቀመጠበት ባዶ የረዳት መስመርን የሚያሳየን ምስል


- ከዚህ በታች የምንመለከተው በG ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ በረዳት መስመሮች ላይ የምናስቀምጣቸው ኖታዎች እና የኖታ ስሞች ናቸው፡፡

በሙዚቃ መፃፊያ ሠልዳ ላይ ከታች እና ከላይ የሚወጡ ኖታዎች እና የኖታዎች ስሞች




ምስል 2.9 በ G ክሌፍ የረዳት መስመር እና ኖታዎች ስም የሚያሳየን ምስል

ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች የምንመለከተው በ F ቁልፍ (clef) የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ የረዳት መስመሮችን ቦታ ይሆናል




ምስል 2.10 በ F ክሌፍ የረዳት መስመር እና ኖታዎች ስም የሚያሳየን ምስል

## 2.2. ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎች

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

**መግቢያ**

ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜ ማለት ሀገራዊ የሆነ ወይም የአንድ አከባቢን ባህላዊ ፣ ሃይማኖታዊ እንዲሁም ክብረ-በዓላዊ ውዝዋዜን መከወን ነው። በሃገራችን በኢትዮጵያ ብዙ አይነት ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎችን እናገኛለን እነዚህን ውዝዋዜዎች በተለያዩ ኩነቶች ልንተገብራቸው እንችላለን።

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- በተለያዩ አካባቢ ያሉትን ሀገረ-ሰባዊ (ባህላዊ) የሰርግ ፣ የለቅሶ ፣ የተለያዩ ክብረ-በዓላትን ውዝዋዜዎች እና እንቅስቃሴያቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳያሉ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- መምህሩ በማህበረሰቡ የተለያዩ ውዝዋዜዎችን ያብራራሉ

- *ተማሪዎች የሚያውቁትን ሀገረሰባዊ ውዝዋዜ እንዲወያዩ በቡድን ከፋፍሎ እንዲወያዩ ያደርጋሉ*
- *የተወያዩትን ነገር በተወካያቸው በኩል እንዲያብራሩ ያደርጋሉ*

***ማነቃቂያ***

- ባህላዊ (አካባቢያዊ) በዓላት ላይ በምን በምን ሁኔታ እንደሚከወን ተወያዩ፡፡

**ፍንጭ**

- *መምህር በአካባቢው የሚዘወተሩ ባህላዊ የሆኑ ክንውኖችን እንዲያቀርቡ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡*

***ጠቃሚ መረጃ***

*ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎችን ልናይ ከምንችልባቸው ኩነቶች መካከል ሰርግ ፣ ለቅሶ እና የክብረ በዓላት ክንዋኔዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡*

***ሀገረ-ሰባዊ የሰርግ ውዝዋዜ*** *በአንድ አካባቢ የሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ የሚታይ ባህላዊ ውዝዋዜ ሲሆን አካባቢን በሚገልፁ ዜማዎች እና ውዝዋዜዎች ሰርጋቸውን የሚያደምቁበት መንገድ ነው፡፡*

***ሀገረ-ሰባዊ የለቅሶ ውዝዋዜ*** *በተወሰነ አካባቢ ታዋቂ ሰዎች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች እንዲሁም የጎሳ መሪዎች ሲሞቱ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ በ ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜ እና ጭፈራ የሚከናወንበት ስርዓት ነው፡፡*

***ሀገረ-ሰባዊ የክብረ በዓል ውዝዋዜ*** *በአንድ አካባቢ የሚከበሩ ባህላዊ የሆኑ ክብረ-በዓላት ላይ ሀገረ-ሰባዊ ውዝዋዜዎችን እናገኛለን፡፡ ይሄ የውዝዋዜ አይነት ለበዓሉ ድምቀትን ለመፍጠር የሚደረግ ክንዋኔ ነው፡፡*

**መልመጃ 2.2**

- ተማሪዎች ሀገረ-ሰባዊ የሆኑ የሰርግ ፣ የለቅሶ እና የተለያዩ አካባቢ ባህላዊ የክብረ-በዓላት ውዝዋዜዎችን በመለማመድ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡

**ፍንጭ**

- መምህር ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ሀገረ-ሰባዊ ክንዋኔዎችን በተውኔት መልክ እንዲያሳዩ ያግዟቸው፡፡

## 2.2.1. የቤተሰብ የአብነት እንቅስቃሴዎችን በመዝሙር እና በውዝዋዜ ማሳየት የመማር ማስተማር ክንውኖች

- መምህሩ የቤተሰብ የአብነት እንቅስቃሴዎችን በዝርዝር ያስረዳሉ
- ተማሪዎች የአብነት እንቅስቃሴዎች የሚባሉትን በመዘርዘር እንዲሳተፉ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ምንያክል እንደተገነዘቡ ለማወቅ ጥያቄ በመጠየቅ ምላሻቸውን ይሰማሉ
- በመጨረሻም አብነት የሆኑ የቤተሰብ እንቅስቃሴዎችን በውዝዋዜ እንዲያሳዩ ያደርጋሉ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች የሚያውቁትን በቤት ውስጥም ሆነ በስራ ቦታ የሚዘወተሩ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን አስታውሰው ለጓደኞቻቸው ያቅርቡ፡፡

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች የሚያስታዉሷቸውን መዝሙሮችና ውዝዋዜዎች በሚያቀርቡበት ጊዜ ክትትል ማድረግ፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የቤተሰብ የስራ መዝሙሮችን መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ ሆኖም ግን አንድ አካባቢ የሚጠቀምበት ግጥም እና ዜማ ከሌላው አካባቢ በተወሰነ መንገድ እንደየባህሉ ሊለያይ ይችላል፡፡ በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ የቤተሰብ የስራ መዝሙሮችን ከእንቅስቃሴዎቻቸው ጋር መግለጽን ይማራሉ፡፡ በቤት ዉስጥ የሚደረጉ የቤተሰብ እንቅስቃሴዎችን በመዝሙር እና በውዝዋዜ ማሳየት የትምህርቱ አካል ነው፡፡ ቤት ውስጥ የሚደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለአብነት ያህል ቤት ዉስጥ ስራ በሚሰራበት ወቅት ማለትም ልብስ ማጠብ ፣ ልጅ ማባበል (ማጫወት). . .ወዘተ መዝሙር በመዘመር ወይም በውዝዋዜ በመግለፅ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ጋር የበለጠ ቁርኝት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ምሳሌ**

## የቤተሰብ ፍቅር




**ምስል 2.11-የቤተሰብ ፍቅር መዝሙር በሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ላይ**

**መልመጃ 2.3**

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚዘመሩ የቤተሰብ መዝሙሮችን በመዘመር ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ።

**ፍንጭ**

- መምህር ተማሪዎች የተለያዩ የቤተሰብ መዝሙሮችን እንዲዘምሩ እገዛ ያድርጉላቸው።

## 2.3. ኮላጅን ለስላሳ/ሸካራ በሆኑ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች መስራት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 8

### መግቢያ

ኮላጅ ማለት የተለያዩ የወዳደቁ ወይም ከአካቢያችን የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመሰብሰብና በመለጠፍ የሚሰራ የስዕል አይነት ነው። ኮላጅ አዳዲስ ፈጠራዎችን ባልተለመደ መልኩ የተለያዩ ባህሪያት ያላቸውን (ሸካራ እና ለስላሳ) ቁሳቁሶች በአንድ ላይ ትርጉም ባለው መልኩ በማሰባጠር ለማቅረብ አይነተኛ መንገድ ነው።

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህን ርዕስ ተምረው ሲጨርሱ ተማሪዎች፡-

- የኮላጅ ስዕሎችን በአካባቢያቸው በሚገኙ ቁሳቁሶች ይሰራሉ
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን እንዴት ወደ ኮላጅ ስዕል መቀየር እንደሚችሉ ይገነዘባሉ

- አካባቢያቸውን የሚበክሉ የወዳደቁ ነገሮችን እንዴት ወደ ስዕል መቀየር እንደሚችሉ ይለማመዳሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ለኮላጅ መስሪያ የሚያገለግሉ የወዳደቁ ቁሳቁሶች
- ኮላ/ሙጫ
- መቀስ
- ማስመሪያ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ስለ ኮላጅ ሥዕል በሚገባ ማስረዳት እና ምሳሌዎችን መጥቀስ
- ተማሪዎች በቡድን ሆነው ኮላጅ ከምን እንደሚሰራ ተወያይተው እንዲቀርቡ ያደርጋል
- በመጨረሻም ተማሪዎች ተወያይተው ያቀረቡትን ሃሳብ ማጠቃለያ ይሰጣል

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ➢ ኮላጅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡


**ፍንጭ**

- ➢ መምህሩ የተማሪዎች ቅድመ ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ለመረዳት ስለ ኮላጅ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረዳት፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ኮላጅ ማለት የተለያዩ የወዳደቁ ወይም በአካባቢያችን የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመሰብሰብና በመለጠፍ የሚሰራ የስዕል አይነት ነው፡፡ ኮላጅ አዳዲስ ፈጠራዎችን ባልተለመደ መልኩ የተለያዩ ባህሪያት ያላቸውን ቁሳቁሶች በአንድ ላይ ትርጉም

ባለው መልኩ በማሰባጠር ለማቅረብ አይነተኛ መንገድ ነው። የኮላጅ ስዕል በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ ሲሆን በዚህ ዘመን ከፍተኛ እድገት ላይ እንደ ደረሰ መገንዘብ እንችላለን። በዚህ ርዕስ ላይ ከመምህሩ የሚጠበቁ ነገሮች ለተማሪዎች የተሻለ ግንዛቤ እና የመፍጠር ክህሎታቸውን ከፍ የሚያደርጉ ምሳሌዎችን በማንሳት በአካባቢያቸው ያለውን እምቅ ግብዓት እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው። ኮላጅ ለመስራት ሽካራ ፣ ለስላሳ ፣ ፕላስቲክ ፣ ጨርቅ ፣ አዝርዕቶችን እንዲሁም ሌሎችን ቁሳቁሶች እንደ ግብዓት ልንጠቀም እንችላለን። ከታች በምስሉ ላይ እንደምንመለከተው ተማሪዎች በቤታቸው የሚገኙ ጥራጥሬዎችን በመጠቀም  የተለያዩ አበባዎችን ፣ የእንስሳትንና የሰዎችን ምስሎች በቀላሉ በኮላጅ ስዕል መስራት ይችላሉ። መምህሩም ተማሪዎች እንደዚህ አይነት በቀላሉ የሚሰሩ ነገሮችን በመጠቀም በተግባር እንዲለማመዱ እና ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል። ብዙ አይነት የኮላጅ አይነቶች ቢኖሩም ግን ለ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የወረቀት እና የፎቶ ኮላጅን መመልከት በቂ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ መምህሩ በእነዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ ያስተምራል።



ምስል 2.12-የተለያዩ ጥራጥሬዎችን በመጠቀም በኮላጅ የተሰራ የነብር ፊት



ምስል 2.13- የወረቀት ኮላጅ



ምስ ል2.14- የፎቶ ኮላጅ

**መልመጃ 2.4**

- ከላይ የተቀመጡትን የኮላጅ ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የሚፈልጉትን የኮላጅ ስዕል በመስራት ያሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎች ምን አይነት ስዕል ሊሰሩ እንደሚችሉ ፍንጭ በመስጠት ክትትል ያደርጋል፡፡

**የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- የተለያዩ ፎቶዎችን እና ወረቀቶችን ከመፅሄትና ከጋዜጣ ላይ መሰብሰብ
- ኮላ/ሙጫ ወይም የስንዴ ሙቅ
- መቀስ
- ጣውላ/ካርቶን
- እርሳስ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎች ሲሰሩ ይመለከታሉ

  በግል ገለፃ እንዲያደርጉ ያደርጋሉ

## 2.4. ቅርፆች፤ ለስላሳነትና ሸካራነት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 5

**መግቢያ**

ለስላሳነት ወይም ሸካራነት በአንድ እቃ ላይ ሊኖር የሚችል ሲሆን በማየት ወይም በመዳሰስ ልንረዳው እንችላለን፡፡ በስዕል ውስጥ ሸካራ ወይም ለስላሳ የቁሳቁስ ባህሪ

ሲሆን እውነተኛ እና ተፈጥሮአዊ ባህሪን ለመግለጽ እንጠቀምበታለን፡፡ በተያያዘም አንድን ነገር ሸካራ ነው ስንል ጥንካሬን እንዲሁም በቀላሉ የማይሰበር እና የጽናት ተምሳሌት መሆኑን ለማሳየት እንጠቀምበታለን፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ለስላሳ ነገሮችን ቶሎ የሚሰበሩና ጥንቃቄ የሚፈልጉ ነገሮችን እንወክልበታለን፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- የእቃዎችን ለስላሳ እና ሸካራ ባህሪያትን ይረዳሉ
- ለስላሳና ሸካራ የሆኑ ስዕሎችን በማስደገፍ ይስላሉ
- የልስላሴና እና የሸካራ አይነቶችን ያውቃሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ለስላሳ እና ሸካራ ቁሳቁሶች
- እርሳስ
- ወረቀት

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ለስላሳ እና ሸካራ የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ በሚገባ ለተማሪዎች ገለፃ ያዳርጋሉ
- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶችን በመንካት እና በማየት ሰካራ እና ለስላሳ መሆናቸውን ምሳሌ ይሰጣሉ
- በመጨረሻም ተማሪዎች ምን ያክል እንደተገነዘቡ ለማወቅ ጥያቄ በመጠየቅ መልስ ይሰጣሉ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን በመንካት እንዲሁም በማየት ለስላሳ እና ሸካራ መሆናቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

**ፍንጭ**

- በጥያቄው መሰረት በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ማለትም መጽሃፍትን ፣ ጠረጴዛዎችን ፣ ግድግዳውን ፣ መስታወቶችን… ወዘተ በመዳሳስ ምን አይነት ባህሪ እንዳላቸው በማየት እንዲሁም በመንካት እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ሸካራ እና ለስላሳ በአንድ እቃ ላይ ሊኖር የሚችል ሲሆን በማየት ወይም በመዳሰስ ልንረዳው እንችላለን፡፡ በስዕል ውስጥ ሸካራ ወይም ለስላሳ የቁሳቁስ ባህሪ ሲሆን እውነተኛ እና ተፈጥሯዊ ባህሪን ለመግለጽ እንጠቀምበታለን፡፡ በተያያዘም አንድን ነገር ሸካራ ነው ስንል ጥንካሬን እንዲሁም በቀላሉ የማይሰበር እና የጽናት ተምሳሌት መሆኑን ለማሳየት እንጠቀምበታለን፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ለስላሳ ነገሮችን ቶሎ የሚሰበሩ ፣ ሊበላሹ የሚችሉ ነገሮችን እንወክልበታለን፡፡ በ4ኛ ክፍል ሁለት አይነት የለስላሳና ሸካራ አይነቶችን ልንመለከት እንችላለን፡፡ በእይታ ብቻ የምንለየው ሸካራነት ወይም ለስላሳነት (visual texture) እና በመዳሰስ የምንለየው እውነተኛ ሸካራነት/ለስላሳነት (real texture) ናቸው፡፡

**መልመጃ 2.5**

- ተማሪዎች ሸካራ የሆኑ ቁሳቁሶች ላይ በማስደገፍ የተለያዩ ዲዛይኖችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው::

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች የተለያየ አይነት ዲዛይንና ሸካራነት ያላቸውን ቁሳቁሶች አስደግፈው በእርሳስ በመፈተግ ወረቀቱ ላይ እንዲወጣ ያድረጉ::

## 2.5. ድምፅ-አልባ ተውኔትና ግለ-ተውኔት (መነባንብ)

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 8

**መግቢያ**

ድምፅ-አልባ ተውኔት እና ግለ ተውኔት በአንድ ሰው ሊሰሩ የሚችሉ የመድረክ ላይ ተውኔቶች ናቸው:: ድምፅ-አልባ ተውኔት ያለ ድምጽ በዝምታ የሚተወን ሲሆን ግለ ተውኔት ግን በድምጽ ፣ በዜማ እና በግጥም መልክ የራሳችንን ስሜት በመጨመር መድረክ ላይ የምናቀርበው ጥበብ ነው:: ድምፅ-አልባ ተውኔትን በምዕራፍ አንድ ስለተመለከትን አሁን ደግሞ ግለ-ተውኔትን (መነባንብን) እንመለከታለን::

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ተማሪዎች ግለ ተውኔትን ይለማመዳሉ
- ግጥም ላይ የራሳቸውን ስሜት ጨምረው መድረክ ላይ በተውኔት መልኩ ያቀርባሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- የመለማመጃ መድረክ/ክፍል
- አልባሳት

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ግለ ተውኔቶችን ያብራራሉ
- በቃላቸው የሚያውቁት ተውኔት ወይም ድራማ ካለ ተማሪዎችን እንዲያቀርቡ ያደርጋሉ

**የግምገማ እና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎች ግለ-ተውኔት ሲያቀርቡ መመልከት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ➢ ከዚህ በፊት ግጥም አንብበው ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ የሚያውቁትን ግጥም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው።

**ፍንጭ**

- ➢ ይህን ጥያቄ መሰረት በማድረግ መምህሩ የተማሪዎችን ስሜት ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ እንዲሁም የፊት ግጽታ በመመልከት ለተማሪዎች ያስረዳሉ።

**ጠቃሚ መረጃ**

ግለ- ተውኔት ከትወና አይነት አንዱ ሲሆን በአንድ ግለሰብ ብቻ የሚሰራ የተውኔት አይነት ነው። አንድ ታሪክን በአንድ ገፀ-ባህሪይ በአንድ ተዋናይ ለተመልካች የምናሳይበት የትወና መንገድ ነው። ግለ-ተውኔት በንግግር መልክ የተፃፈ ግጥም ነው። ነገር ግን ሲቀርብ ግጥማዊ ይዘቱ እና ዜማው ጠፍቶ

በተውኔት መልክ የሚቀርብ ነው፡፡ ተዋናዩ ታሪኩን በመወከል ስሜትን በመጨመር ታሪኩን እውነተኛ ለማስመሰል ይተውናል፡፡ ግለ ተውኔት በሶስት ይከፈላል፡፡ እርሱም ድራማዊ መነባነብ ፣ ሶኪሎክና የውስጥ መነባነብ ናቸው፡፡

### 2.5.1. ድራማዊ መነባንብ

በግለሰብ መልክ በአንድ ገፀ-ባህሪ ንግግር የተፃፈ ግጥም ነው፡፡ የታሪኩ ባለቤት ምንነት ፣ ስነ ልቦና እና ስሜትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በአንድ ገጸ-ባህሪ ድምፅ አልባ በሆነ መንገድ የሚተወን የተውኔት አይነት ነው፡፡ ይህንን አይነት ግለ-ትወና ለመስራት በመጀመሪያ የታሪኩን መነሻ እና ባህሪ ፣ የራሳችንን ፍላጎት እና ምን አይነት የስሜት መውጣት እን መውረድ እንደሚያስፈልገው በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ መምህሩም ተማሪዎችን ግለ ተውኔት እንዲለማመዱ ሲያደርግ በመጀመሪያ ተማሪዎችን ስለ ታሪኩ በሚገባ እንዲያውቁ ማስተማር ይገባዋል፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች በሚሰሩት ግለ-ተውኔት ውስጥ ምን አይነት ስሜቶች (ለምሳሌ የማልቀስ ፣ የማሳዘን ፣ የደስታ ፣ የመናደድ… ወዘተ) እንደሚያስፈልጉ በደንብ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሁለት አይነት የመነባንብ አይነቶች አሉ፡፡ እነርሱም ሶኪሎክ መነባንብ እና የውስጥ መነባንብ ናቸው፡፡ ሶኪሎክ መነባንብ አንድ ገፀ-ባህሪ ሃሳቡን ወይም ስሚቱን ጮክ ብሎ የሚገልጽበት የትወና አይነት ሲሆን የውስጥ መነባንብ ደግሞ በድራማ ውስጥ ገፀ-ባህሪው የራሱን ማንነት ፣ ፍላጎቱን እና በውስጡ ያለውን ስሜት ወይም ጥያቄ ብቻውን ሆኖ የሚተርክበት የግለ-ተውኔት አይነት ነው፡፡

**መልመጃ 2.6**

- ተማሪዎች ከዚህ በታች ያለውን መነባንብ የራሳቸውን ስሜት እና እንቅስቃሴ ጨምረውበት ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- ሙሉ ግጥሙ መማሪያ መጽሀፋቸው ላይ ስለሚገኝ መምህሩ መድረክ ላይ ወጥተው እንዲያሳዩ ያድርግ፡፡

## 2.5.2. ተውኔቶችን ለተመልካች ማቅረብ

ተማሪዎች የሰሯቸውን ተውኔቶች በተመልካቾች ፊት በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ማቅረብ ለሌላ ተጨማሪ ተውኔት ስለሚያነሳሳ መለመድ ያለበት ተግባር ነው፡፡ ተውኔቶችን በቀላሉ ተመልካቾች ፊት እንዲደርሱ ተዋንያን ሁል ጊዜ ወደ ተመልካቾች በማዞር መስራት አለባቸው፡፡ ሁል ጊዜ ተመልካቾች ፊታችን ላይ የሚፈጠረውን ስሜት ማየት ስላለባቸው ፊት ለፊት ቆመን የትወናውን መልዕክት በቀላሉ ይረዱታል፡፡ መድረክ ላይ ወይም በክፍል ውስጥ ለተመልካቾች ጀርባችንን ከሰጠን ማስተላለፍ የፈለግነው ድራማ ፣ ግጥም ወይም መነባንብ ለተመልካች በትክክል ሳይደርስ ይቀራል ማለት ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ ድምፃችን ለሁሉም ተመልካች መሰማት መቻል አለበት፡፡ ቀስ ባለ ድምጽ መድረክ ላይ ካቀረብን ማስተላለፍ የሚገባንን መልዕክት ላናስተላልፍ ስለምንችል መምህሩ ሁልጊዜ ተማሪዎች ተውኔት ከማቅረባቸው በፊት ከፍ ባለ ድምፅ ማቅረብ እንዳለባቸው ማስታወስ አለበት፡፡ በተለይ ድምፅ-አልባ ተውኔቶችን በምናቀርብበት ጊዜ በተውኔቱ መካከል በስህተት ንግግር እንዳናስገባ መጠንቀቅ ይገባል፡፡ ተመልካቾች በተውኔቱ ቢስቁ እንኳን ተዋናዩ በምንም ሁኔታ መሳቅ የለበትም፡፡ መምህሩም ተማሪዎችን ይህንን እንዳያደርጉ በደንብ ማለማመድ እና ማስታወስ

ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ ነገሮች ከተሟሉ መድረክ ላይ የሚቀርበው ተውኔት በትክክል መልዕክቱ እንዲተላለፍ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 2.7**

- ተማሪዎች የተለያዩ በአካባቢያቸው የሚገኙ ትውፊታዊ ፉከራዎችን ፣ ሽለላዎችን እንዲሁም ቀረርቶዎችን በግጥም ወይም በመነባንብ መልክ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎችን የተለያዩ በአካባቢያቸው የሚገኙ ትውፊታዊ ፉከራዎችን ፣ ሽለላዎችን እንዲሁም ቀረርቶዎችን በግጥም ወይም በመነባንብ መልክ ጽፈው እንዲመጡ እና ሌሎች ተማሪዎች ፊት ግለ-ተውኔት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሁለት ስለ ግለ-ተውኔቶች (መነባንብ) መድረክ ላይ እንዴት እንደሚቀርብ ተመልክተናል፡፡ አንድ ግለ-ተውኔት ለተመልካቾች ስናቀርብ የምናሳየው የስሜት እና የሰውነት እንቅስቃሴን ከመነባነቡ ጋር ማዋሃድ እንዳለብን ተመልክተናል፡፡ የኮላጅ አሰራር እና የኮላጅ አይነቶችን እንዲሁ በስፋት ተመልክተናል፡፡ ሁለት አይነት የኮላጅ አይነቶችን ተመልክተናል፡፡ እነርሱም የወረቀት ኮላጅ እና የፎቶ ኮላጅ ናቸው፡፡ ሃገረሰባዊ ውዝዋዜዎች ከዜማዎች ጋር በመዋሀድ መዝሙሮችን ለመዘመር እንደሚያግዝም አይተናል፡፡ በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ የሙዚቃ ቁልፎችን እና ኖታዎችን እንዴት መፃፍ እንደሚቻል በስፋት ለመመልከት ችለናል፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የኮላጅ አይነቶችን እነዲዘርዝሩ ያድረጉ
2. ተውኔቶችን ለተመልካች ለማቅረብ ምን እንደሚያስፈልግ ይጠይቋቸው
3. ሳንቲሞችን አስደግፈው የተለያዩ ዲዛይኖችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው
4. ስለ ቤተሰቦቻቸው የራሳቸውን ግጥሞች በመጻፍ በመዝሙር መልክ ይለማመዱ
5. ከዚህ በታች በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ (ስታፍ) ላይ ያሉትን የኖታ ስሞች ይለዩ



ምስል 2.15 የሙዚቃ መፃፍያ ሴሌዳ

**መልስ**

1. ሁለት የኮላጅ አሰራር አይነቶች ይገኛሉ፡፡ እነርሱም የፎቶ ኮላጅ እና የወረቀት ኮላጅ ናቸው፡፡ የፎቶ ኮላጅ የምንላቸው የተለያዩ ፎቶዎችን በመቆራረጥ እና በመገጣጠም ሌላ አይነት ምስል ለመፍጠር የሚያግዘን ሲሆን የወረቀት ኮላጅ የምንለው የተለያየ ቀለም ያላቸውን ልሙጥ ወረቀቶች በመገጣጠም ምስል የምንፈጥርበት የኮላጅ አሰራር አይነት ነው፡፡
2. ተውኔቶችን ለተመልካች ለማቅረብ መጀመሪያ ታሪኩን በደንብ መሸምደድ ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ለታሪኩ የሚያስፈልጉ አልባሳትን እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም በተመልካች ፊት ለማቅረብ ደጋግሞ መለማመድ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡
3. በዚህ ርዕስ ተማሪዎች አስር ፣ ሃምሳ ፣ አንድ ብር እና ሌሎችን ሳንቲሞች በማስደገፍ ወደ ወረቀት በእርሳስ ላይ ያትሙታል ማለት ነው፡፡
4. ስለ ቤተሰቦቻችሁ የራሳችሁን ግጥሞች በመጻፍ በመዝሙር መልክ ይለማመዳሉ
5. በኖታ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ የተፃፉ የኖታ ምልክቶችን ለይተው እንዲያነቡ መምህሩ እገዛ ያደርጋሉ

| ምዕራፍ ሶስት | 3.የትውን እና የእይታ ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ<br>ለምዕራፉ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 20 |
|---|---|

## መግቢያ

ስነ ጥበብ በሰዎች የዕለት ከዕለት ኑሮ ዉስጥ የሚጫወተው ሚና ጉልህ ነው፡፡ የትውን እና እይታ ጥበባት ደግሞ የማህበረሰቡን ንቃተ-ህሊና ከፍ ለማድረግ ሙዚቃዊ ፣ ስዕላዊ እንዲሁም ድራማዊ በሆነ አቀራረብ እውቀትን ለማሸጋገር ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ማህበረሰቡም የማድነቅና አዲስ ነገር የመፍጠር ተነሳሽነቱን ለመጨመር ኪነ-ጥበብ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ስዕል ፣ ሙዚቃ ፣ ትያትር እንዲሁም ተውኔት ሰዎችን ከማሳቀ እንዲሁም ከማዝናናት ባሻገር ቁም ነገር ያዘሉ ነገሮችን በቀላሉ ለማስተላለፍ አይነተኛ መንገዶች ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ስለ አካባቢያቸው ፣ ስለ ተፈጥሮ እንዲሁም ሌሎች አንገብጋቢ ጉዳዮችን በማንሳት በቀላሉ ግንዛቤ ወደ ማህበረሰቡ እንዲሰርፅ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

በዚህ የ4ኛ ክፍል መጽሐፍ ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ቲያትር ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ለማንሳት ያስፈለገበት ምክንያት ተማሪዎች ነገሮችን በቀላሉ ስዕላዊ እና ሙዚቃዊ በሆነ መንገድ እንዲረዱ እና የፈጠራ ችሎታቸውን ለማሳደግ እንዲያግዛቸው ለማድረግ ነው፡፡ የአንድን ማህበረሰብ እድገት ለማፋጠን ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ለዚህም ደግሞ ማህበረሰባዊ ስዕልን (community art) ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች የተለያዩ ታሪካዊ ፣ ባህላዊ እና አካባቢያዊ ቅርሶችን ስነ-ጥበብን በመጠቀም ይገልጻሉ
- ታሪካዊ ቦታዎችን ይጎበኛሉ
- ተማሪዎች ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይረዳሉ
- ለሰላም ፣ ለሃዘን ፣ ለደስታ እንዲሁም ለሃገር የተዘመሩ መዝሙሮችን ያውቃሉ
- አካባቢያዊ ጥበቦችን በመጠቃም መዝሙሮችን ፣ ድምፅ-አልባ ተውኔቶችን ፣ ውዝዋዜዎችንና ግለ-ተውኔቶችን ይከውናሉ
- የሚታወቁ ሀገረሰባዊ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይማራሉ
- ምልክቶችን ፣ የቤተሰቦቻቸውንና የጓደኞቻቸውን የልብስ ቀለማት እንዲሁም የሃገራቸውንና የክልላቸውን የባንዲራ ቀለማት ለይተው ያውቃሉ

## ለምዕራፉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የመለማመጃ አዳራሽ/ክፍል
- አካባቢያዊ የሆኑ የድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻዎች ፣ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች … ወዘተ
- የድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስል መሳሪያዎች
- እርሳስ ፣ ባለ ቀለም ጠመኔ (ክራዮን) እና ሌሎች በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶች

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- መምህሩ በአካባቢያቸው ያሉ ታሪካዊ ቅርሶችን ያብራራሉ፣ ምሳሌም ይሰጣሉ
- ሙዚቃና ሥዕል ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጥቅም ያስረዳሉ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- በምልከታ
- በግላዊ ገለፃ
- በቡድን ገለፃ
- በማህደር
- በቃል ጥያቄ

## 3.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በማህበረሰቡ ታሪክና ባህል ያለው ሚና መግቢያ

የትውን እና እይታ ጥበብ ለአንድ ማህበረሰብ እድገት ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታን ያበረክታል። የትውን እና እይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ ባህል እድገት እንዲሁም ታሪክን ጠብቆ ለማቆየትና ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ትልቅ ሚና አለው። ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት ለአንድ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ጠቀሜታዎችን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ተማሪዎች ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ቲያትር የሚያበረክተውን ሚና ያውቃሉ
- የትውን እና የእይታ ጥበባት የማህበረሰቡን ታሪክ እና ባህል ከመጠበቅ አንፃር የሚያበረክተውን ጠቀሜታ በሚገባ ይረዳሉ
- ስነ-ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያውቃሉ
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ሃገረሰባዊ ጥበቦችን እና ታሪካዊ ቅርሶችን እና ባህሎችን ያውቃሉ
- ስነ-ጥበብ ለአንድ ማህበረሰብ የባህል እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ያውቃሉ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የትውን እና የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበርክተውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ
- ተማሪዎች የተገነዘቡትን ለማወቅ ጥያቄ በመጠየቅ ምላሽ ያገኛሉ

**የማነቃቂያ ተግባራት**

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ባህላዊ እና ታሪካዊ የሆኑ እሴቶችን በምን አይነት ሁኔታ እንደሚገልጹ ይናገሩ/ ያሳዩ
- ከዚህ በፊት በአካባቢያቸው የሚያውቁት ሰዓሊ እና ስዕል በመሸጥ የሚታወቅ ሰዓሊ ካለ ለክፍል ጓደኞቻቸው ይናገሩ።

**ፍንጭ**

- በዚህ ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች የትውን እና እይታ ጥበባትን በመጠቀም የፈለጉትን ባህላዊ እንቅስቃሴ በስዕል ፣ በሙዚቃ እና በግለ-ተውኔት መልክ እንዲያቀርቡ መምህሩ ያበረታታቸው።
- መምህሩ ተማሪዎችን ስዕል ስለሚሰጠው የገቢ ምንጭ ከማስተማሩ በፊት በአካባቢያቸው ያሉ ሰዓሊዎችን እንዲዘረዝሩ እና ገቢ እንዴት እንደሚያገኙ እድል በመስጠት እንዲነቃቁ ያደርጋል።

### 3.1.1. የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ጠቀሜታ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 7

## ሀ. ስነ-ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ፎቶ እና ተንቀሳቃሽ ምስሎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ሥዕል ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በሚገባ ያብራራሉ
- መምህሩ ተማሪዎችን ምሳሌዎችን እንዲጠቅሱ በማድረግ ውይይት ያደርጋሉ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- አካባቢያቸውን እንዲመለከቱ በማድረግና ያዩትን ሲያብራሩ መመልከት
- የባህል እና ቅርስ ቤተ-መዘክሮችን እንዲመለከቱ በማድረግ

**ጠቃሚ መረጃ**

ስነ-ጥበብ ባህልንና እሴትን ከማስተዋወቅ በተጨማሪ የገንዘብ ምንጭ ይሆናል። በየአካባቢያችን ያሉትን ቤተ-መዘክሮች ፣ የባህል ማዕከሎች እንዲሁም የስዕል መሳያ ቦታዎችን ብናስፋፋ ከሚፈጠረው የስራ እድል በተጨማሪ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር ዜጎች መጥተው ሊያዩ ፣ ሊገዙ እንዲሁም ሊዝናኑበት ይችላሉ።

ለምሳሌ በደቡብ ብሄር ብሄረቦችና ህዝቦች ክልል የጋሞ የባህል ማዕከል ፣ የኮንሶ ህዝቦች ሙዝየም ፣ የወላይታ ጉታራ የባህል ማዕከል ፣ የጉራጌ ባህል ማዕከል … ወዘተ ባህልን ከማስተዋወቅ ባሻገር ለገንዘብ ማስገኛ ከፍተኛ የቱሪዝም ምንጭ እንዲሆኑ በደንብ ማስተዋወቅ እና መስራት ይቻላል። መምህሩም ተማሪዎችን

በየአካባቢያቸው የሚገኙትን የስነ-ጥበብ ማዕከላትና ሌሎችንም በየአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች በቡድን እንዲያወያዩ እና ማብራሪያ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

**መልመጃ 3.1**

- በአካባቢያቸው ቤተ መዘክሮች ወይም የባህል ማዕከሎች ካሉ በውስጣቸው ስላሉ ቅርሶች ወይም ስዕሎች ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ፡፡

**ፍንጭ**

- ተማሪዎችን በአካባቢያቸው የሚገኝ የባህል ማዕከል ወይም ቤተ-መዘክር ካለ በውስጡ ያሉ ነገሮችን በመዘርዘር እንዲያመጡ እድሉን ያመቻቻል ፣ በክፍል ውስጥ ማብራርያ እንዲያደርጉ በማገዝ ውጤት ይሰጣል፡፡

## ለ. ስነ ጥበብ የማህበረሰቡን ባህል እና እሴት ከመጠበቅ አንፃር የሚያበረክተው ጠቀሜታ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ታሪካዊ ስዕሎች እና ፎቶዎች
- የተቀረጹ ተውኔቶች ወይም ተንቀሳቃሽ ምስሎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ተማሪዎችን በቡድን በማድረግ ሥዕል ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ እንዲወያዩ በማድረግ በተወካያቸው በኩል ማብራርያ እንዲሰጡ ያደርጋሉ
- መምህሩ ተማሪዎችን በየቡድኑ በመሄድ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ያቀረቡትን መሰረት በማድረግ ማጠቃለያ ይሰጣሉ

## የግምገማና ክትትል ስልት

- ፎቶዎችን እና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በማሳየትና ግብረ-መልስ እንዲሰጡ በማድረግ
- የግል ምልከታዎቻቸውን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ እና ነጥብ መስጠት

## ጠቃሚ መረጃ

እንደ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ብዝሀነትን በአንድ ክልል እንደሚያተናግድ ማህበረሰብ ሰዎች ባህላቸውንና ማንነታቸውን ለማሳየት ስነ-ጥበብ ጉልህ አስተዋፅኦ አለው:: ስነ-ጥበብ በቡድንም ሆነ በግል ውበት ጎልቶ እንዲወጣ ያግዛል:: ለምሳሌ ሴቶች በጋብቻ ወቅት አምሮባቸው እንዲታዩ ከሚለብሱት ልብስ ጀምሮ እንደየ ባህላቸው ለመዋቢያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ይህም ማለት የቀለማት መርጫዎቻችን ፣ የልብስ ዲዛይኖቻችን እንዲሁም የምንጠቀምባቸው ጌጣጌጦች ሁሉ በእያንዳንዳችን ባህል የምናከናውናቸው የዕለት ከዕለት ተግባሮቻች ናቸው:: ቀለማት ባህላችንን ስለሚያንጸባርቁ እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱ የሚወደውና የሚወክለውን ቀለም እንደመገለጫ አድርጎ በልብስ መልክ ፣ በባንዲራ እና በቤት ውስጥ በሚገኙ ቁሳቁሶች ላይ ሊጠቀም ይችላል:: ለዚህ ደግሞ የወላይታንና የጋሞን ድንጉዛ ፣ የጉራጌን ቀሚስ ፣ የአሪ በሄረሰብን የኮይሻ ቀሚስ... ወዘተ የራሳቸው ቀለም እና ዲዛይኖችን እንዴት እንደሚጠቀሙበት ማየት እንችላለን:: ለዚህም በተጨማሪ የቤት አሰራር ጥበቦቻችን ፣ የሸክላ ስራዎቻችን ፣ የሽመና እና የብረታብረት ስራዎቻችን የምንሰራበት መንገድ የውበትን ጽንሰ-ሃሳብ የምንረዳበት አረዳድ እንደባህላችን ስለሚለያይ ነው:: መምህሩ ከላይ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ስነ ጥበብ ለባህላቸው ምን ያክል ጠቀሜታ እንዳለው ተማሪዎች በቡደን ሆነው እንዲወያዩ እና እንዲያብራሩ ማድረግ አለበት:: መምህሩ በዚህ ርዕስ ስር ስነ-

ጥበብን በመጠቀም ባህላቸውን እንዲያስተዋውቁ እንዲሁም በባህላቸው እንዲኮሩ በማድረግ ያስተምራሉ::

**መልመጃ 3.2**

- ተማሪዎች በቡድን በቡድን በመሆን ከራሳቸው ባህል ውጭ የሚያውቁትን የሌሎች ማህበረሰቦችን የአለባበስ ፣ የአመጋገብ እና የአኗኗር ሁኔታ ያሳዩ/ይናገሩ::

**ፍንጭ**

- ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በሚኖሩበት አካባቢ የሌሎች ማህበረሰቦችን አለባበስ አነጋገር እና ባህል ያዩትን እንዲያሳዩ እድሉን ይሰጣቸዋል:: የዚህ ጥያቄ ዋናው አላማ ተማሪዎችን ከራሳቸው ባህል ውጭ ምን ያክል እንደሚያውቁ ለመገንዘብ ነው::

## ሐ. ሃገረሰባዊ እውቀትንና ስልጣኔን ለማዳበር

### የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ቀደምት ስልጣኔዎችን ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት
- የምልክት ቋንቋዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች

### የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ሀገረሰባ እውቀቶች ማብራሪያ ይሰጣሉ
- ጥያቄ በመጠየቅ ምላሽ ያገኛሉ

## የግምገማ እና ክትትል ስልት

- ተማሪዎች የተለያዩ ሃገረ-ሰባዊ ስልጣኔዎችን የሚያሳዩ ስዕላዊ በሆነ መንገድ ሰርተው እንዲያመጡ በማድረግ መገምገም
- በቀላሉ ለመግባቢያነት የሚያገለግሉ ምልክቶችን ሰርተው እንዲያመጡ በማድረግ መገምገም/ውጤት መስጠት

## ጠቃሚ መረጃ

ስነ-ጥበብ ውስጣዊ ስሜታችንን አውጥተን እንድናሳይ ስለሚያግዘን በጋራ የመስራት እና ማህበራዊ መሰረቶቻችንን ያጠናክራል። በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ እውቀቶችን በማውጣት የመናገር ፣ የማስታወስ እና የመፍጠር ችሎታችንን ለማዳበር ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ትውፊታዊ ስዕሎችን የሚሰሩ ሰዓሊያንንም ለማበረታት ያግዛል። ትውፊታዊ ስዕሎችን የሚስሉ ስንል በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በትምህርት ሳይሆን በራሳቸው ጥረት ያገኙትን እውቀት የማህበረሰቡን እሴት እና እውነተኛና ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚስሉትን ለማበረታታት ያግዛል። በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩትን የአካል ጉዳተኞችን ተሳታፊ ለማድረግ ስነ-ጥበብ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ለምሳሌ መናገር እና መስማት የማይችል ሰው ሃሳቡን በስዕል ሊገልጽ ይችላል። መስማት የማይችልን በስዕል ፣ ማየት የማይችል በሙዚቃ ፣ መናገርም ሆነ መስማት የማይችልን ሰው ደግሞ በንክኪ ነገሮችን እንዲገነዘብ ለማድረግ የትውን እና እይታ ጥበባት ትልቅ ሚና አላቸው።

ስነ-ጥበብ ባህልን ለማስተዋወቅ ጉልህ ሚና አለው። ለምሳሌ በደቡብ ኦሞ የሚገኙ የተለያዩ ብሄረሰቦች ማለትም የሀመር ፣ ሙርሲ ፣ ባና ፣ ኛንጋቶም እና የአሪ ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ ሃገረሰባዊ የመዋቢያ እና የጌጣጌጥ መጠቀሚያዎች አሏቸው። ወንዶችና ሴቶች ሰውነታቸው ላይ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን የአፈር

አይነቶች በጥብጠው በመቀባት ባህላዊ ውዝዋዜውችን በቡደን ሆነው ሲጨፍሩ እጅግ ውብ ድምቀትን ይፈጥራሉ። ወዝዋዜዎቻቸውም በሙዚቃ ፣ በስዕል እንዲሁም ድራማዊ በሆነ መንገድ ስለሚቀርብ ባህልን ከማስተዋወቅ ጎን ለጎን ለገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላል።

ፎቶ የቅርብንም ሆነ የሩቅ ጊዜን በተጨባጭ መረጃዎች ለማስደገፍ ስለሚያግዝ ቦታን ፣ ጊዜን እንዲሁም ሁኔታዎችን ለማስታወስ አይነተኛ መንገድ ነው። ለምሳሌ በጋሞ ባህል መሰረት ግጭት በተፈጠረ ሰዓት ለማስቆም እርጥብ ሳር ወይም ጨፌ ይዞ ከፊት ከቆመ በሁለቱም ወገን ግጭቱን ውዲያውኑ ያቆማሉ። ከታች ያሉት ፎቶዎችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በክርክር ፣ በድራማ ወይም በሙዚቃ መልኩ ሊገልጿቸው ይችላሉ። የመምህሩም ድርሻ ተማሪዎች ሌሎች ተጨማሪ ፎቶዎችን እንዲያመጡና ማብራሪያ እንዲያቀርቡ መድረኩን ማመቻቸት ይሆናል።



ምስል 3.1- የጋሞ ሽማግሌዎች ግጭትን የሚያስቆሙበት መንገድ

**መልመጃ 3.3**

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ሰዓሊዎች የተለያዩ ቀለሞችን እንዴት እንደሚያዘጋጁ በመጠየቅ ሰርተው ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ፡፡

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ታሪካዊ እና ባህላዊ ነገሮችን በመጎብኘት ወይም ሰዎችን በመጠየቅ ስላዩት እና ስለሰሙት ነገር ጽፈው በክፍል ውስጥ ያንብቡ፡፡

**መ. ታሪካዊ ቅርሶችን መጎብኘት**

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ታሪካዊ ጉዞዎችን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ የጉዞ ቁሳቁሶች
- ታሪካዊ ፎቶዎች እና ተንቀሳቃሽ ምስሎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ቅርሶችን ከቻሉ ሄደው በማየት፤ መጎብኘት ካልቻሉ ደግሞ በፎቶ በማሳየት ማብራሪያ እንዲያደርጉ ያግዟቸው

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎች ያዩትን ነገር እንዲያንጸባርቁ በማድረግ
- አካባቢያቸውን እንዲመለከቱ በማድረግ እና ጥያቄ በመጠየቅ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት ጎብኝተው የሚያውቁትን ቅርስ ለክፍል ጓደኞቻቸው ይናገሩ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ወይም ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሄደው የጎበኟቸው ቅርሶች ካሉ ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያደርጋል፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ታሪክን ለመገንዘብ ስነ-ጥበብ አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ከዛሬ አምስት መቶ አመት በፊት ስለነበረው የሰው ልጆች ታሪክና የአኗኗር ሁኔታ ለመገንዘብ በስዕል በፎቶ እንዲሁም በቅርፃ ቅርፅ መልክ የተቀመጡ ነገሮችን እንደ ትልቅ ማስረጃ ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡ ከፎቶዎቹ በመነሳትም የሰዎችን የኑሮ እንዲሁም የስልጣኔ ደረጃዎችን መገንዘብ እንችላለን፡፡ ታሪካዊ ቅርሶችን መጎብኘት በአካባቢያችን ያሉትን ነገሮች እንድናውቅ እድሉን ይሰጠናል፡፡ ለምሳሌ የጥያ ትክል ድንጋይን ስንመለከት የጥንት ሰዎች ምን አይነት ስራ እንደሰሩ በድንጋይ ላይ ጽፈው አስቀምጠዋል፡፡ የጥያ ትክል ድንጋይ መካነ መቃብር ላይ ለመታሰቢያነት የሚቆም ሲሆን ድንጋዩ ላይ የተለያዩ ምልክቶች ፣ የሰዎች ምስሎች ፣ ጎራዴ እና ልዩ ልዩ የሆኑ ጌጣጌጦች ተስለውበት ማየት እንችላለን፡፡

**መልመጃ 3.4**

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታሪካዊ እና ባህላዊ ነገሮችን በመጎብኘት ወይም ሰዎችን በመጠየቅ ስላያችሁት እና ስለሰማችሁት ነገር ጽፋችሁ ወይም ስላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- በዚህ ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች የተለያዩ ቀለማቶችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ ንጥረ ነገሮች እንዲያዘጋጁ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ቀይ፣ ጥቁር፣ ነጭ፣ ቢጫ እንዲሁም አረንጓዴ ቀለሞችን እዲያዘጋጁ ያደርጋል፡፡

## ሠ. ምልክቶችን፣ የሃገራችንን እና የክልላችንን የባንዲራ ቀለማት የቤተሰቦቻንንን እንዲሁም የጓደኞቻችንን የልብስ ቀለማት መለየት

### ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ወቅታዊ ሁኔታን ለማስተማር የሚያገለግሉ ምልክቶች
- ተማሪዎች አርዓያ የሚያደርጓቸው ሰዎች ፎቶግራፎች
- የተለያዩ ቀለሞች
- እርሳስ
- ወረቀት

### የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በየአካባቢው የሚገኙ ቀለማቶችን ማብራሪያ ይሰጣሉ
- የሚወዱትን ቀለም ይናገራሉ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች የምትወዱት ቀለም ምንድን ነው? ለምን እንደወደዳችሁት ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ይህን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ተማሪዎችን ስለ እለቱ ትምህርት እንደ መግቢያ ይጠቀሙበት፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ቀለም የአንድን ማህበረሰብ አኗኗር ባህል እና እሴት አጉልቶ ለማሳየት ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ አንድ ማህበረሰብ ደስታውን ሃዘኑን እንዲሁም መንፈሳዊ ህይወቱን በተለያዩ ቀለማቶች ይገልፃል፡፡ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እያንዳንዳችን የምንወደና የማንወደው ቀለም በውስጣችን ሊኖር ይችላል፡፡ ለመውደዳችንም ይሁን ለመጥላታችን መንስኤ የሚሆናው የምንኖርበት አካባቢ ፣ ያደግንበት ባህል እንዲሁም ሌሎች ምክንያቶች ሊኖሩን ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን የቀለማት ምርጫችን በምንኖርበት ማህበረሰብ ላይ ተመስርቶ እናገኘዋለን፡፡ የህፃናት የቀለም ምርጫ ከአዋቂዎች ይለያል፡፡ ብዙ ጊዜ የህፃናት የቀለም ምርጫቸው ደማቅ የሆነ ቀለም (ቢጫ ፣ ሰማያዊ ፣ ቀይ) ሲሆን አዋቂዎች ደግሞ ደብዘዝ ያሉ ቀለማትን (ነጭ እና ጥቁርን ጨምሮ) በብዛት ያዘወትራሉ፡፡ ህፃናትን አልባሳት ለመግዛት የልብስ መሸጫ ሱቅ/መደብር አስገብተን እንዲመርጡ ብናደርጋቸው መጀመሪያ የሚመርጡት ልብስ የሚወዱት ቀለም ነው ማለት እንችላለን፡፡ የቀለም ምርጫችን እንደየ እድሜ ደረጋጃችንም ጭምር የተለያየ ነው፡፡ ነጭ ቀለምን ከሌሎች ቀለማቶች ጋር በማሰባጠር በብዙ የሃገራችን ባህላዊ አልባሳት ላይ ይጠቀሙበታል፡፡ የከፋ ፣ ሃድያ ፣ የወላይታ ፣ የጉራጌ ፣ የአሪ ፣

… ወዘተ የባህል ልብሶች ውስጥ ነጭ ቀለምን ከሌሎች ቀለማቶች ጋር በመቀላቀል ባህላዊ ልብሶችን በመስራት ያስውባሉ፡፡

ስነ-ጥበብን የምንጠቀምበት ስዕል ብቻ ለማስተማር ሳይሆን ተጓዳኝ ማህበራዊ፡ ፖለቲካዊ እንዲሁም  ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በማንሳት ለማስተማርና በቀላሉ መልዕክትን ማስተላለፍ ስዕል እንዳንረሳው ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ የተያዩ ስዕሎችን በመጠቀም ስለ አካባቢ ንጽህና፡ስለ ኮሮና ቫይረስ ፣ ስለ ኤች አይ ቪ አኤድስ እንዲሁም ተያያዥ ወቅታዊ ጉዳዮችን በስዕል፤ በቅርፃ ቅርፅ እንዲሁም በፖስተር መልክ መልዕክቶችን ማስተላለፍ እንችላለን፡፡ የተለያዩ ስዕላዊ መልዕክቶችን መንገድ ዳር ፣ በእምነት ቦታዎች ፣ በሆስፒታሎች ፣ በትምህረት ቤት ውስጥ እንዲሁም በልዩ ልዩ ቦታዎች በማስቀመጥ መልእክቶችን በቀላሉ ማስተላለፍ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ ከታች በምስሉ ላይ ያለውን ምልክት ልጆች በቤታቸው ውስጥ፤ በትምህርት ቤታቸው ፣ እንዲሁም በመኖሪያ አካበቢያቸው ስእላዊ መግለጫዎችን በመለጠፍ ማስክ በማድረግ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በቀላሉ መልክቶችን ማስተላለፍ እንችላለን፡፡

**መልመጃ 3.5**

- በአካባቢያችሁ በበዓላት ወቅት ሰዎች በብዛት የሚለብሷቸው የቀለም አይነቶችን እና ምክንያታቸውን ዘርዝሩ፡፡
- ተማሪዎች በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የሚገኙ ምልክቶችን እያስታወሳችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን ምልክቶች በመሳል ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ከመግባታቸው በፊት ብትምህርት ቤታቸው ውስጥ የተለጠፉ ምልክቶችን እንዲያስታውሱ በማድረግ ቀስ በቀስ ወደ እለቱ ርዕሰ ጉዳይ እንዲገቡ ያድርግ
- ተማሪዎች በየአካባቢያቸው የሚዘወተሩ ማለትም በደስታ ፣ በሃዘን ፣ በሰርግ እና በልዩ ልዩ በዓላት ወቅት የሚለበሱ የልብስ ቀለማትን ትርጉም እንዲዘረዝሩ ያደርጋል። በተጨማሪም በሌሎች አካባቢዎች የተለመዱ የልብስ ቀለማትን እና ትርጉማቸውን እንደምሳሌ በመጥቀስ ለተማሪዎች ያስረዱ።
- ተማሪዎችን የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን ስዕሎች በመሳል እንዲለማመዱ መምህሩ እገዛ ያደርግላቸዋል

### 3.1.2. ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 7

**መግቢያ**

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ይረዳሉ። ይህም ሙዚቃ የአንድን ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ፣ ባህል ፣ እምነት እና የዕለት ከዕለት የኑሮ ሁኔታን አጉልቶ ለማሳየት የሚኖረውን ጠቀሜታ እንገነዘባለን።

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች ሙዚቃ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይረዳሉ
- ለሰላም ፣ ለሃዘን ፣ ለደስታ እንዲሁም ለሃገር የተዘመሩ መዝሙሮችን ያውቃሉ
- አካባቢያዊ እውቀቶችን በመጠቀም መዝሙሮችን ይዘምራሉ
- የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎች ይረዳሉ
- ሙዚቃን ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ጋር አብሮ በማጣመር የኑሮአችን አንዱ መገለጫ ማድረግ እንችላለን፡፡ ሙዚቃ በእለት ከእለት የኑሮ እንቅስቃስያችን የደከመን አእምሯችንን ለማሳረፍ ፣ ስነ-ቃሎችን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም የሃገር ፍቅርን ለመግለጽ ያግዛል፡፡

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- እባክዎት መምህር ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለ ስራ ፣ ስለ ሃገር እንዲሁም ስለ ተፈጥሮ የተዘመሩ/የተዘፈኑ ዘፈኖችን በማምጣት በክፍል ወስጥ እንዲዘምሩ አርድኋቸው፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ?

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎች በደንብ ሊያውቁት እና ሊዘምሩት የሚችሉንት ስለ ሃገር የተዘመረ መዝሙር እንደ መንደርደሪያ በማድረግ ወደ ርዕሱ ያልፋሉ፡፡ ለምሳሌ አርማችን ነው መለያችን የሊትዮጵያ ሀገራችን፣ ፀሐየ ዮሀንስ <u>ማን እንደ እናት ማን እንደ ሀገር…</u> ወዘተ የሚለውን ዘፈን ማዘማር ይችላል፡፡
- ይህ ጥያቄ መምህሩ ተማሪዎችን ስለ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ያላቸውን ቅድመ መረዳት ለመገመት ያገለግላል፡፡ የተማሪዎችን ምላሽ መሰረት በማድረግ መምህሩ በሃገረሰባዊ የሙዚቃ መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን ያስተምራሉ፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ሙዚቃ ህብረተሰቡን ስለ አካባቢያቸው ባህል ፣ ወግ እንዲያውቁ በማድረግ ትልቅ ሚናን ይጫወታል:: ሙዚቃ አእምሮን ከማነቃቃት እና ከማዝናናት በተጨማሪ ባህልን ፣ ወግን ፣ እና የኑሮ ሁኔታን ብግጥም እና በዜማ መልክ በማዋሃድ ለረጅም ዘመናት እንዲቆይ የማድረግ አቅም አላው:: ሙዚቃ ከኮንሰርት አዳራሽ ባሻገር የማህበረሰቡን የደስታ ፣ የሃዘን ፣ የስራ እንዲሁም ባህል እሴቶችን ለመጠበው ጉልህ ድረሻ አለው::

ሙዚቃን ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ጋር አብሮ በማጣመር የኑሮአችን አንዱ መገለጫ ማድረግ እንችላለን:: ሙዚቃ በእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃስያችን የደከመን አእምሯችንን ለማሳረፍ ፣ ስነ-ቃሎችን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም የሃገር ፍቅርን ለመግለጽ ያግዛል::

**መልመጃ 3.6**

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለ ስራ ፣ ስለ ሃገር እንዲሁም ስለ ተፈጥሮ የተዘመሩ/የተዘፈኑ ዘፈኖችን በማምጣት በክፍል ወስጥ ዘምሩ::

**ፍንጭ**

- እባክዎት መምህር የመረጡትን መዝሙር በህብረት እንዲዘምሩ ያግዛቸዋል::

## ሀ. አከባቢያዊ ጥበቦችን በመጠቀም መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን መከወን

**ጠቃሚ መረጃ**

አከባቢያዊ ጥበቦች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የተሰሩ እና የተለመዱ ባህላዊየሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚሰሩ ዜማዎችን ለማወቅ ያግዘናል:: ለምሳሌ ክራር ፣ መሰንቆ ፣ ዲታ ፣ ከበሮ ፣ ዲንክያ (ድንካ) ፣ ባህላዊ የውዝዋዜ

አልባሳት እና የተለያዩ ለባህላዊ ክንውኖች በመጠቀም የሚደረግ ሙዚቃዊ ተግባር ነው። ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በምንጫወትበት ጊዜ ትክክለኛውን የባህል አልባሳት በመልበስ ውዝዋዜዎች በግልም ሆነ በቡድን በማድረግ ደማቅ ትርኢት ለማሳየት ይጠቅማል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህላዊ ዘዴዎችን በመጠቀም አከባቢያዊ ሙዚቃዎችንና ውዝዋዜዎችን የሚከውኑ ማህበረሰቦች ይገኛሉ። ከነዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ለአብነት ያክል በዳውሮ ማህበረሰብ ከሚጠቀሟቸው አከባቢያዊ የሙዚቃ መሳሪያ አንዱ ድንካ በመባል ይታወቃል። ድንክያ በቁመቱ ረዘም ያለ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን በቡድን በመሆን የሚጫወቱት የባህላዊ መሳሪያ ነው። ድንክያን በሚጫወቱበት ጊዜ አብሮ የሚያጅብ ከበሮ ይገኛል። ከበሮን ከስልተ-ምት የሙዚቃ መሳሪያ ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ምቱን ጠብቆ ከድንክያ ጋር ይጫወቱታል። ድንካ የሚሰራው ከአከባቢው በሚገኘው ግብዓት ሲሆን ከቀርካሃ ፣ ከከብት ቀንድ (ከጎሽ ቀንድ) እና ለውበት የሙዚቃ መሳሪያው (ድንክያው) ጫፍ ላይ ትንሽ የከብት ቆዳ ይታሰርበታል።

**መልመጃ 3.7**

- በሀገራችን በኢትዮጵያ የተለያዩ አከባቢያዊ ሙዚቃዎችን እናገኛለን፡፡ ከዚህ በመነሳት ተማሪዎች በቡድን በመሆን በአከባቢያችሁ የሚገኙ ባህላዊመዘሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ዝግጅቶቻቸውን እንዲያቀሩ ያደርጋል፡፡ ሙዚቃውን ካቀረቡ በኂላ በጥሩ ሁኔታ ያቀረበውን ቡድን ያደንቃል ያበረታታል፡፡ በመጨረሻም ያቀረብቡትን ሙዚቃ መሰረት በማድረግ ውጤት ይሰጣል፡፡

## ለ. የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊዘፈኖችንና ውዝዋዜዎች መከወን

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- በአካባቢያችሁ የሚታወቁ ባህላዊ ዘፈኖችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቁችን ባህላዊ ዘፈኖችን እንዲዘፍኑ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

ሃገረሰባዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያየ ወቅት የሚደረጉ ዜማዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ዜማዎች በስራ ጊዜ ፣ በሰረግ ፣ በለቅሶ እንዲሁም በበዓላት ጊዜ የሚዘፈኑ ናቸው፡፡ የዘፈኖቹ ሁኔታ እንደ ማህበረሰቡ የኑሮ እና የባህል ልዩነት በተለያየ መንገድ ይከናወናሉ፡፡ መምህሩ ተማሪዎችን

በአካባቢያቸው የሚገኙ ሃገረሰባዊ መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን እንዲያውቁ ያደርጋል። ብዙውን ጊዜ የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ (ባህላዊ ዘፈኖችን) የሚባሉት በቤተሰብ ፣ በጎሳ ፣ በማህበረሰብ ወይም በሌላ ቅርብ በሆነ ቡድን አውድ ውስጥ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ማለትም ስራ በሚሰራበት ወቅት ፣ እርሻ በሚታረስበት ወቅት እና በመሳሰሉት በደቦ ለስራ በሚሰባሰቡበት ጊዜ የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይማራሉ።

**መልመጃ 3.8**

- ተማሪዎች በአከባቢያቸው ማህበረሰብ በስራ እና በተለያዩ ክንውኖች የሚጠቀሟቸውን የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ ውዘወዋዜዎችንና ዘፈኖችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎችን በአካባቢያቸው የሚገኙ የተለያዩ ባህላዊ ክንዋኔዎች ላይ የሚዘፈኑትን ዘፈኖች በክፍል ውስጥ እንዲዘምሩ ያድርጓቸው።

## 3.1.3. የትውን ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጠቀሜታዎችን እንመለከታለን። የእይታ ጥበብ ድራማን ፣ ትያትርን እንዲሁም ግጥማዊ መነባንቦችን በመጠቀም ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ማስተላልፍ እንችላለን። ተማሪዎች

በአካባኢያቸው ላይ የሚመለከቱዋቸውን ባህላዊ ክንዋኔዎችን ፣ ማህበራዊ ችግሮችን እንዲሁም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን በድራማ ፣ በትያትር እንዲሁም በመነባብብ መልኩ ማሳየት ይችላሉ፡፡ የትውን ጥበባት ከንግግር እና ከጽሁፍ ባለፈ ሰዎችን እየተዝናኑ ቁምነገር እንዲጨብጡ ለማድረግ አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ ፣ በትምህርት ቤታቸው አካባቢ እንዲሁም በእምነት ተቋማት አካባቢ የተመለከቱዋቸውን ሁኔታዎች እንደ መነሻ ሃሳብ በመውሰድ ተውኔቶችን ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**መልመጃ 3.9**

- ተማሪዎች በምትኖሩበት አካባቢ በባህላዊ መንገድ ሰዎችን እንዴት እንደሚያስታረቁ አጭር ድራማ በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ

**ፍንጭ**

- በጥያቄው መሰራት መምህሩ ተማሪዎችን የተለያዩ ባህላዊ የእርቅ ስነ-ስርዓቶችን በመጠቀም የተጣሉ ሰዎችን እንዴት እንደሚያስታርቁ በድራማ ያሳያሉ

## ማጠቃለያ

መምዕራፍ ሶስት የዕይታ እና የትውን ጥበባት ለማበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ተመልክተናል። ሙዚቃ ፣ ስዕል ፣ ትያትር ፣ ድራማ እና ፎቶግራፍ የአንድን ማህበረሰብ የታሪክ ፣ የባህል ፣ እንዲሁም የአስተሳሰብ ደረጃን ለማሳየት ትልቅ ሚና አላቸው። ይህም ማለት ባህልን ለመጠበቅ እንዲሁም ለማስተዋወቅ ፣ ታሪክን ለመመዝገብ እና ለማጥናት ትልቅ አስተዋጻኦ አለው። ስለዚህ የዕይታ እና የትውን ጥበባትን ከማህበረሰቡ የእለት ተእለት ኑሮ ነጥለን ማየት አንችልም።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. ተማሪዎች የተለያዩ አከባቢዎችን ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩዋቸው
2. በአከባቢያችሁ የሚገኝ አከባቢያችሁን የሚገልፅ የትንፋሽ፣የስልተ-ምት፣የክር የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጫዎት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩዋቸው
3. የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጥቅም ዘርዝሩ
4. የትውን ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

## መልስ

1. ተማሪዎች በአካባቢያቸው የተለመዱ ውዝዋዜዎችን እና ዜማዎችን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ እድል መስጠት
2. ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የትንፋሽ የሚዚቃ መሳሪያዎችን ልክ እንደ ከበሮ ፣ ዋሽንት ፣ ፊላ እንዲሁም ጥሩምባ ያሉ መሳርያዎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ
3. የእይታ ጥበብ ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጠቀሜታ መካከል ታሪካዊ ቅርሶችን ለመጎብኘት ፣ ተጓዳኝ ነገሮችን ለማስተማር ያገለግላል እና ባህልን እና እሴትን ለመጠበቅ ያግዛል
4. የትውን ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ሚና መካከል ታዋቂ ሰዎችን አስመስሎ ለመጫወት ፣ ታሪክን ለመአስተማር ወዘተ

| ምዕራፍ አራት | 4.አድናቂነት<br>ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 22 |
| --- | --- |

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የትውን እና የእይታ ጥበባት ማድነቅን ፣ መለማመድን እና መገምገምን በስፋት እናያለን፡፡ ሃገር በቀል እውቀቶችን በማድነቅ በተለያዩ የእይታና የትውን ጥበባት ውስጥ መለማመድ እና ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ስዕልን ፣ ሙዚቃን ፣ ትያትርን እና ስነ-ጽሁፍን ደጋግመው ሲለማመዱ የሚያገኙትን ጥቅም እንዳስሳለን፡፡ ስልጣኔ ማለት የነበረውን ሃገረሰባዊ እውቀት በሌላ ሃገር ባህል መተካት ሳይሆን የነበረውን እውቀት ደግፎና ተንከባክቦ ማሳደግ ስለሆነ በአካባቢያችን የሚገኙ ሃገረሰባዊ እውቀቶችን ለማሳደግ ከማድነቅ እንጀምራለን፡፡

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ -

- ሃገር በቀል እውቀቶችን ያደንቃሉ
- መዝሙሮችንና ውዚዋዜዎችን ደጋግመው መለማመድ የሚያመጣውን ውጤት ይረዳሉ
- ስለ ሀገር በቀል የሙዚቃ ጫዋታዎች በሚገባ ይረዳሉ
- ፎቶ ማንሳት ይለማመዳሉ
- ግለ-ተውኔት/መነባንብ ያቀርባሉ/ይጽፋሉ
- ሃገረሰባዊ የቤት አሰራር አይነቶችን ያውቃሉ

## ለምዕራፉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የመለማመጃ አዳራሽ/ክፍል
- አካባቢያዊ የሆኑ የድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫዎቻዎችን ፣ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች … ወዘተ
- የድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል መሳሪያዎች
- እርሳስ ፣ ባለቀለም ጠመኔ (ክራዮን) እና ሌሎች በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶች

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ተማሪዎች ግለ ተውኔቶችን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያደርጋሉ
- ሥዕልን ደጋግመው ሲለማመዱ ክትትል ያደርጋሉ
- ሙዚቃን እና ውዝዋዜዎችን ደጋግመው በመለማመድ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳያሉ:: መምህሩም አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ

## የግምገማና ክትትል ስልት

- ተማሪዎች የተግባር ስራዎችን ሲሰሩ በማየት
- ስለተረዱት ነገር ግላዊ ገላፃ ሲያደርጉ በመስማት
- በቡድን የሰሩትን ነገር ገላፃ ሲያደርጉ በመስማት
- የተማሪዎችን ማህደር በማየት
- የቃል ጥያቄ በመጠየቅ
- ሀገረሰባዊ የሆኑ ሙዚቃዎችን ተማሪዎች ሲያቀርቡ በመከታተል እና ደጋግመመው እንዲለማመዱ ያድርጉ

## 4.1. የትውን እና የእይታ ጥበባት በአፈፃፀምና በምስል ጥበባት ውስጥ የመለማመድ ውጤት

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ስር የተለያዩ ድራማዎችን ፣ መነባንቦችን እንዲሁም ግጥሞችን ደጋግመን በመለማመድ እንዴት መድረክ ላይ ማቅረብ እንደምንችል እንማራለን። ደጋግሞ መለማመድ ወደ እንከን የለሽ ብቃት ስለሚያሳድግ ተማሪዎች ይህንን ተረድተው እንዴት መለማመድ እንዳለባቸው እንመለከታለን ።

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች የእይታና የትውን ጥበባትን ደጋግመው ይለማመዳሉ
- ስዕልን ፣ ሙዚቃንና ተውኔትን ደጋግመው በመለማመድ የሚያገኙትን ጥቅም ይረዳሉ
- የእይታ ጥበባትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያውቃሉ
- ደጋግመው በመለማመድ ችሎታቸውን ያሳድጋሉ
- ችግር ፈቺ ጥናቶችን እና ምርምሮችን በመስራት ይለማመዳሉ
- ደጋግመው በመስራት በራስ መተማመናቸውን ያዳብራሉ
- ተማሪዎች ድራማን እና ትያትርን ደጋግሞ በመለማመድ ችሎታቸውን ያዳብራሉ
- በራስ መተማመናቸውን ያዳብራሉ
- ተማሪዎች መዝሙሮችንና ውዝዋዜዎችን ይለማመዳሉ
- መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን በተደጋጋሚ በመለማመድ ችሎታቸውን ያዳብራሉ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ የምትሰሩትን ስዕል ለመምህራችሁ ተናገሩ ወይም የሳላችሁትን አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ከላይ በተጠቀሰው የማነቃቁያ ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ደጋግመው የተለማመዱትን ስዕል እንዴት በአጭር ጊዜ እንደሚስሉትና ችሎታቸውን እንደሚጨመረላቸው ማሳየት አለባቸው፡፡ ወይም ተማሪዎችን ሰርተው እንዲያሳዩ ማድረግ አለባቸው፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ስዕልን ደጋግሞ መስራት ፍጹም ያደርጋል እንደሚባልው ሁሉ አንድን ኪነ-ጥበባዊ ክንዋኔ በተደጋጋሚ በተለማመድን ቁጥር የማድረቅ አቅማችን በዚያው ልክ እናሳድጋለን፡፡ የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ እንደሚባለው አባባል በደንብ ያልተለማመድነውን ድራማ ወይም ሙዚቃ መድረክ ላይ ብናቀርብ ሊበላሽብን ወይም ልናፍርበት እንችላለን ማለት ነው፡፡ መምህሩም ተማሪዎችን በተደጋጋሚ እንዲለማመዱ እና ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ይድርግላቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስዕልን ሙዚቃን እና ድራማን ደጋግሞ መለማመድ የሚሰጠውን ጥቅም ሰፋ በማድረግ ለተማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ ስዕልን በተደጋጋሚ ለረጅም ጊዜ ለመስራት ከፈለጉ ሁልጊዜ ከቀላል ወደ ከባድ መሄድ እንዳለባቸው መግለጽ ይስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ ቀላል መስመሮችን በማስመር ወደ ንድፍ ስዕል እንዲያሳድጉ እንገልጽላቸዋለን፡፡ አንድን ነገር አይተን የመሳል/የመንደፍ ችሎታችንን ካዳበርን በኋላ ቀላል ቀለማቶችን እንዴት መቀባት

እንድምንችል እናሳያቸዋለን። በመቀጠል ደግሞ የቀለማቶቹን ባህሪያት ለመረዳት ቀለም እንዴት እንደሚቀላቀሉ እና እንደሚቀቡ ደግሞ በሂደት እናስገነዝባቸዋለን። እንዲህ እንዲህ እያልን መስራት የሚፈልጉትን የስዕል አይነት ለመስራት ደረጃ በደረጃ የስነ-ጥበብ አይነቶችን እናስተምራቸዋለን ማለት ነው። መምህሩ ሙዚቃንም ሆነ ድራማን ከላይ እንደጠቀስነው ደረጃ በደረጃ በተደጋጋሚ በመለማመድ የሚፈልጉትን ችሎታ እንዲያዳብሩ ማገዝ ይችላሉ።

**መልመጃ 4.1**

የእይታ እና የትውን ጥበባትን ደጋግሞ በለማመድ የሚያስገናቸውን ጥቅሞች ዘርዝሩ።

**መልስ**

- የእይታ እና የትውን ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ ችሎታን ለመጨመር ፣ ተውኔቱን በቃል ሸምድዶ ለመያዝ ፣ እንዲሁም ሙዚቃዎችን በደንብ ለመጫዎት ያግዛል።

### 4.1.1. የእይታ ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 8

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- የስዕል መለማመጃ ክፍል
- ወረቀት
- ቀለም
- እርሳስ
- ብሩሽ
- ፓርከር

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ተማሪዎች አንድን ስዕል በክፍል ውስጥ ደጋግመው ሲለማመዱት እየተከታተሉ ድጋፍ ያደርጋሉ
- በትክክል መሳላቸውን ለማረጋገጥ ዞረው ይመለከታሉ
- ስለሳሉት ሥዕል ማብራሪያ ይሰጣሉ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ልጆቹ ሲለማመዱ በማየት ይገመግማል
- በግልም ሆነ በቡድን የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን እንዲሰሩ በማድረግ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች የመረጡትን የስዕል አይነት አምስት ጊዜ ደጋግማችሁ ሳሉት:: አምስቱን ስዕሎች በማወዳደር የተሻለውን ምረጡ::

**ፍንጭ**

- ከላይ የተገለጸውን የየማነቃቂያ ጥያቄ መሰረት በማድረግ መምህሩ ተማሪዎችን የፈለጉትን ስዕል አምስት ጊዜ ደጋግመው እንዲስሉ ያደርጋል:: ከሳሏቸው ስዕሎች መካከል የተሻለውን እንዲመርጡ እና ደጋግመው በመሳላቸው ችሎታቸውን ምን ያክል እንዳሻሻሉ በማሳየት ወደ እለቱ ትምህርት መንደርደሪያ ሀሳብ ያገኛሉ ማለት ነው::

**ጠቃሚ መረጃ**

ሥዕል መስራት የሚጀመረው ከመሞነጫጨር ሲሆን ወደ ትላልቅ የሸራ ላይ ስዕል እና ቅርፃ ቅርፅ ያድጋል:: ስዕል መሳል በአንድ ቀን ወይም በአንድ ወር የሚለመድ ሳይሆን በሂደት ለወራት አለዚያም ለአመታት ተለማምደን የምናገኘው

ችሎታ ነው፡፡ ሥዕልን ደጋግሞ በመለማመድ የተማሪዎችን ችሎታ ለማዳበር ትልቅ ሚና አለው፡፡ ሥዕል መስራት የሚጀመረው ከመሞነጫጨር ሲሆን ወደ ትላልቅ የሸራ ላይ ስዕል እና ቅርፃ ቅርፅ ያድጋል፡፡ ስዕል መሳል በአንድ ቀን ወይም በአንድ ወር የሚለመድ ሳይሆን በሂደት ለወራት አለዚያም ለአመታት ተለማምደን የምናገኘው ችሎታ ነው፡፡ ሥዕልን ደጋግሞ በመለማመድ የሚከተሉትን ጥቅሞች እናገኛለን፡፡

- ችሎታችንን እናሳድጋለን
- ችግር ፈቺ ፈጠራዎችን እንሰራለን
- እንዝናናለን
- በራስ መተማመናችንን እናዳብራለን

**መልመጃ** 4.2

ተማሪዎች አንድን የድመት ስዕል አምስት ጊዜ ደጋግማችሁ በመሳል ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

➢ በዚህ ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች የድመትን ስዕል ደጋግመው በመሳል የሚያሳዩትን የችሎታ ለውጥ በመገምገም፡፡

### 4.1.2. የትውን ጥበባትን ደጋግሞ መለማመድ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ለድራማ/ተውኔት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች
- የመለማመጃ ክፍል/አዳራሽ

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ከዚህ በፊት ተማሪዎች ስለሰሩት ድራማ እንዲያወሩ እድል ይሰጣል
- ከተማሪዎች ሃሳብ ከተቀበሉ በኋላ ማጠቃለያ ይሰጣሉ

## የግምገማና ክትትል ስልት

- ተማሪዎች ሲለማመዱ በመመልከት
- ተማሪዎች ተውኔቶችን ሲያቀርቡ ባሳዩት ስቃት በመገምገም

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- *ተማሪዎች ከዚህ በፊት ድራማ ሰርታችሁ ታውቃላችሁ? ሰርታችሁ ከሆነ ከማቅረባችሁ በፊት ስንት ጊዜ ተለማመዳችሁት? ለጓደኞቻችሁ አስረዱ።*

**ፍንጭ**

- *መምህሩም ተማሪዎችን ድራማውን ለስንት ጊዜ እና በምን አይነት መንገድ እንደተለማመዱት ተማሪዎች እንዲያብረሩ እድል ይሰጣል።*

## ጠቃሚ መረጃ

የትውን ጥበባት ከሚባሉት ውስጥ ሙዚቃ እና ትያትር (ድራማ) ዋነኞቹ ናቸው። አንድን ሙዚቃ ወይም ድራማ መድረክ ላይ ከማቅረባችን በፊት ለብዙ ጊዜ ደጋግመን እንለማመደዋለን። ድራማ ለመስራት የተለያዩ አልባሳትን ከማሰባሰብ ጀምሮ የድራማውን ዋና ዋና ሃሳቦች በቃላችን (ያለምንም ወረቀት) መሸምደድ መቻልን ያጠቃልላል። ተማሪዎች የሸመደዱትን ነገር ደግሞ እንዳይጠፋባቸው እና ለተመልካቾች በምን አይነት ተውኔት ማሳየት እንዳለባቸው ደጋግመው ማሰብና መለማመድ ይጠይቃል። ሌላው ደጋግሞ የመለማመድ ጥቅም መድረክ ለማቅረብ

ፍርሃት ካለባቸው እንዲያስወግዱ ያግዛቸዋል። አንድ ጀማሪ ሰው ለመጀምሪያ ጊዜ ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ድራማ ሲያቀርብ ፍርሃት ሊታይበት ይችላል። ስለዚህ በራስ መተማመንን ለማዳበር ደጋግሞ መለማመድ ትልቁ መፍትሄ ነው። ተማሪዎች ተውኔቶችን ደጋግመው በሚለማመዱበት ጊዜ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያገኛሉ።

- ጊዜን ለመቆጠብ
- ወጭን ለመቀነስ
- የድራማውን ጭብጥ በደንብ ለመገንዘብ

**መልመጃ 4.3**

1. አንድን ድራማ በትክክል ሳንለማመድ መድረክ ላይ በማቅረብ ብንሞክር ምን አይነት ጉዳት እንዳለው ተወያይታችሁ አቅርቡ?
2. በደንብ ሳይለማመዱ ድራማ ሲያቀርቡ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ፍንጭ**

1. አንድን ድራማ ከማቅረባችን በፊት በደንብ ሳንለማመድ መድረክ ላይ ብናቀርብ መሃል ላይ ሊጠፋብን ይችላል። ስለዚህ የምንፈልገውን ሃስብ ለመግለጽ እንቸገራለን ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሌላ ጊዜ ለማቅረብ እንፈራለን ወይም በራስ መተማመናችን ይጠፋል ማለት ነው።
2. በዚህ ጥያቄ ላይ ደግሞ ተማሪዎች የገጠማቸውን ነገሮች እንዲያካፍሉ ለማድረግ ስለሆነ መምህሩ ለተማሪዎች እድል ይሰጣል።

### 4.1.3. መዝሙርን እና ውዝዋዜን ደጋግሞ የመለማመድ ውጤት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 8

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ለወላጆች በዓል ግጥም እና ውዝዋዜ አቅርባችሁ ከሆነ እንዴት እንደተለማመዳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎችን የወላጆች በዓል እና ልዩ ዝግጅቶች ላይ ያቀረቡት ወዝዋዜ ካለ እንዲያስታውሱ ያግዛቸዋል፡፡

በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች መዝሙርን እና ውዝዋዜን ደጋግመን በመለማመዳችን የምናገኛቸውን ጥቅሞች እንማራለን፡፡ መዝሙር እና ውዝዋዜ በባህሪው ብዙ ልምምድ የሚጠይቅ በመሆኑ ችሎታችንን ለማሳደግ ደጋግመን ብንለማመድ የምናገኘውን ጥቅም እንረዳለን፡፡ ልጆች መዝሙርን የሚለማመዱት ከህፃንነታቸው ጀምሮ ነው፡፡ ይህ ማለት መዝሙርን መለማመድ የሚጀምሩት ከመስማት ሲሆን በአካባቢያቸው የሚታወቁ እናየ ተለመዱ መዝሙሮችን በመዘመር ይለማመዳሉ፡፡ ልጆች መዝሙርን መስማት የሚጀምሩት እናታቸው ወይም አባታቸው እንዲተኙላቸው ፣ ምግብ እንዲበሉላቸው ፣ እንዳያለቅሱባቸውና እንዲጫወቱላቸው ለማድረግ ነው፡፡ መዝሙሮች በህፃናት አዕምሮ ውስጥ መቀረፅ የሚጀምሩት ገና በለጋነታቸው ነው፡፡ ድምጽ እና መዝሙር ቀስ በቀስ ወደ ውስጣቸው በማስገባት ይዘምራሉ ይለማመዳሉ፡፡ ከዝማሬ በተጨማሪው

ዝዋዜዎችንም በአካባቢያቸው ከሚገኙ የሰዎች፣ የእንስሳት እንዲሁም የዕፅዋት እንቅስቃሴ በመነሳት ማስመሰል እና መለማመድ ይጀምራሉ፡፡

**መልመጃ 4.4**

- ተማሪዎች የተለያዩ መዝሙሮችንና በቡድንና በግል በመሆን ውዝዋዜዎችን ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎችን በሚገባ እንዲለማመዱ በቂ ጊዜ በመመደብ አለበት፡፡ ከመዝሙሩ በተጨማሪ ተማሪዎች ደጋግመው በመለማመድ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሙያዊ ትዕግስት እንዲረዱ ለማድረግ ነው፡፡

## 4.2. ሀገር በቀል የቤት አሰራርን እና ማስጌጥን ፣ የሙዚቃ ጨዋታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 6

**መግቢያ**

የቤት አሰራር አይነቶች የአንድን ማህበረሰብ ባህል እና የኑሮ ሁኔታ በከፊል ያሳያሉ፡፡ በሃገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ አይነት የቤት አሰራር አይነቶች እና ስም አላቸው፡፡ ስለሆነም የቤት አሰራር አይነቶች እንደ አካባቢው ባህል ፍላጎት ወይም ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራሮችን ምሳሌ በማንሳት እንማራለን፡፡ ሀገረ-ሰባዊ የሙዚቃ ጨዋታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት ባህላችንን ለማወቅ እና በባህላችን እንድንኮራ ስለሚያደርገን በሚገባ ልናውቀው ይገባናል፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- በአካባቢያቸው እና በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶችን ይረዳሉ
- ሀገር በቀል እውቀቶችን ያደንቃሉ
- ተማሪዎች ፎቶ ማንሳት ይለማመዳሉ
- የተለያዩ ስዕሎችን በመሳል ይለማመዳሉ
- በመዝሙር እና ውዝዋዜ ስለ ሀገራቸው ባህልና ወግ በሚገባ ይረዳሉ
- ሀገር በቀል የሙዚቃ ጨዋታዎችን ያውቃሉ፣ ይዘምራሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶች ፎቶዎች ወይም ስዕሎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶችን እንዲዘረዝሩ ያደርጋሉ
- በአካባቢያቸው የተለመዱትን የቤት አሰራሮች ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እንዲዘረዝሩ ያደርጋሉ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- የጎጆ ቤት እና የቆርቆሮ ቤት ልዩነት ምንድን ነው? አብራሩ፡፡

**ፍንጭ**

- ከላይ ያለውን ጥያቄ ተማሪዎች ስለ ጎጆ እና ቆርቆሮ ቤት አሰራር አይነቶች ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ቤቶቹ እንዴት እንደሚሰሩ፣ ከምን እንደሚሰሩ እና ልዩነታቸው ምን እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ሀገረሰባዊ የቤት አሰራር አይነቶች እንደየ ባህላችን፣ የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የአየር ፀባይ ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ ደጋማ (ቀዝቃዛ) በሆኑ አካባቢዎች የሚሰሩት የቤት ዲዛይኖች ቅዝቃዜን ለመቋቋም (ሙቀትን እንዲፈጥር) ተደርጎ ሲሰራ፣ ቆላማ (ሞቃታማ) በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ በቂ ነፋስ እንዲገባ ታሳቢ በማድረግ ብዙ መስኮቶች እና ቀዳዳዎች እንዲኖሩት ተደርጎ ይሰራል፡፡ አብዛኛው የደቡብ ኦሞ አካባቢዎች በጣም ሞቃታማ በመሆኑ የቤት አሰራር አይነቶች በቀላሉ የሚሰሩ ጎጆዎች ሲሆኑ ነፋስ ወደ ውስጥ እንዲገባ በማሰብ ግድግዳዎቹ ክፍት ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ በተቃራኒው ደጋማ በሆኑ የሃድያ እና የወላይታ አካባቢዎች ደግሞ ሙቀት ከቤት ውስጥ እንዳይወጣ አፍኖ ለማቀረት ሲባል ትንሽ የሆኑ በርና መስኮቶች ያላቸው ሲሆን በአብዛኛው ደግሞ ዙሪያቸውን በጭቃ የተመረጉ ወይም በስሚንቶ የተገነቡ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

**መልመጃ 4.5**

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙ የቤት አሰራሮችን ስላችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- በጥያቄው መሰረት ተማሪዎችን በአካባቢያቸው የሚገኙ የቤት አሰረር አይነቶችን በቀለምም ሆነ በእርሳስ ስለው እንዲያሳዩ ያደርጋል፡፡

### ሀ. ፎቶ ማንሳት መለማመድ

ተማሪዎች ፎቶ ማንሳት እንዲለማመዱ ማድረግ የተፈለገበት የማየት እና የማስታወስ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት መምህሩ ተማሪዎች ፎቶዎችን ማንሳት እንዲለማምዱ ያደርጋል፡፡

### ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የፎቶ ማንሻ ካሜራ

### የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ተማሪዎች ፎቶ ማንሳት ይለማመዳሉ
- ተማሪዎች ያነሷቸው ፎቶዎች ትክክል መሆናቸውን በማየት ያረጋግጣሉ
- ተማሪዎች ያነሷቸውን ፎቶዎች በመመልከት ማጠቃለያ ይሰጣሉ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- የፎቶ ማንሻ ካሜራ በእጃችሁ ይዛችሁ ወይም ፎቶ አንስታችሁ ታውቃላችሁ? ልምዳችሁን ለሌሎች ተማሪዎች አካፍሉ።

**ፍንጭ**

- በዚህ ጥያቄ መምህሩ ፎቶ ተማሪዎችን ፎቶ ማንሳት እንዲላማመዱ ከማድረጋቸው በፊት ስለ ፎቶ ማንሻ ካሜራ ያላቸውን ግንዛቤ በመለካት እንዲያግዘው ለማድረግ ነው።

## ጠቃሚ መረጃ

ፎቶ ለማንሳት መሰረታዊ የፎቶግራፍ አላባውያንን ማለትም ብርሃን ፣ ቀለም ፣ አወቃቀር እና እንቅስቃሴን በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል። ፎቶ ለማንሳት የፎቶ ካሜራ ወይም ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ልንጠቀም እንችላለን። ፎቶ ማንሳት ከመጀመራችን በፊት የምንጠቀምበትን የፎቶ ማንሻ መሳሪያ በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል። መሰረታዊ ከምንላቸው ውስጥ ካሜራ (የስልክ ፎቶ ማንሻ) እንዴት ማብራት እና ማጥፋት እንዳለብ ፣ የካሜራውን ብርሃን እንዴት ማብራትና ማጥፋት እንዳለብን ፣ እንዴት ማቅረብና ማራቅ እንዳለብን እና እንዴት ማንሳት እንደምንችል ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ናቸው።

**መልመጃ 4.6**

➢ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ወይም በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ያሉ ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ፎቶ በማንሳት ተለማመዱ።

**ፍንጭ**

➢ በዚህ ጥያቄ መሰረት መምህሩ ተማሪዎችን ቀላል የሆኑ ፎቶዎችን ማንሳት እንዲለማመዱ ያድርግ። ትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በካሜራ ወይም በተንቀሳቃሽ ስልክ አማካኝነት እንዲለማመዱ አድርጉ።

**ለ. ከፎቶ ላይ ሥዕል መስራት መለማመድ**

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- የተለያዩ ለስዕል የሚሆኑ ፎቶዎች ወይም ስዕሎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ተማሪዎች እንዴት ከፎቶ ላይ ሥዕል መስራት እንደሚችሉ ያስረዳሉ
- ሥዕልን ደግሞ ለማሳል የሚከተሉትን ቅደም ተከተል ያስረዳሉ
- ተማሪዎች የሰሩትን ሥዕል በመመልከት አስተያየት ይሰጣሉ
- የሰሩትን ሥዕል በመመልከት ወጤት ይሰጣሉ

**የግምገማ እና ክትትል ስልት**


- ተማሪዎች የሰሩትን ስዕል በማየት

## ጠቃሚ መረጃ

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች ፎቶዎችን በመሳል ለመለማመድ ነው፡፡ በመጀመሪያ የስዕል ችሎታን ለማዳበር ፎቶዎችን እያዩ ደግሞ በመስራት ወይም የታዋቂ ሰዓልያንን ስዕል ድግሞ በመስራት መለማመድ ይቻላል፡፡ ቀስ በቀስ ግን የራስን የፈጠራ ስዕል በመስራት  ችሎታችንን ማዳበር እንችላለን፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሌላ ሰው የሰራውን ስዕል ደግመን በመሳል የማስመሰል ችሎታችን እናዳብራለን፡፡

## መልመጃ 4.7

ከታች በምስሉ ላይ የሚታይትን ሥዕሎች አስመስላችሁ ሳሉ



ምስል 4.1- ከፎቶ ላይ ስዕል መስራት

## ሐ. የተዘጋጀ ህትመት

### ወረቀት ላይ ቆርጦ በማውጣት ማተም

ይህ የህትመት አይነት የተዘፋጀው ወረቀት ላይ በመንደፍ ቀለም እንዲነካ የሚፈለገውን የወረቀት ክፍል ቆርጦ በማውጣት ቀሪውን የወረቀት ክፍል ደግሞ

በመተው የሚሰራ ነው:: በመቀጠል ደግሞ የተቆረጠው ወረቀት ስር ሌላ ወረቀት በመደረብ ቀለም በነካ ስፖንጅ ወይም ጨርቅ ባዶ ቦታው ላይ ቀስ በሎ ወለም በመቀባት እስኪደርቅ ጠብቆ በማንሳት ህትመቱን በአዲስ ወረቀት ላይ ማሳየት እንችላለን::



ምስል 4.2- የተዘጋጀ የወረቀት ህትመት

**መልመጃ 4.8**

- ተማሪዎች ትላልቅ ድንች ይዛችሁ በመምጣት የምትፈልጉትን ንድፍ ሰርታችሁ ወረቀት ላይ ማተም ተለማመዱ

ፍንጭ

- መምህር እባክዎት ተማሪዎችን ድንች ይዘው እንዲመጡ በማድረግ የድንች ህትመት እንዲለማመዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው

## 4.2.1. ሀገር በቀል የሙዚቃ ጫወታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች የምትወዱት የሃገራችን ሙዚቃ/መዝሙር የቱ ነው? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ፍንጭ**


- በጥያቄው መሰረት ተማሪዎች የሚወዷቸውን ሃገረሰባዊ ሙዚቃዎች እንዲዘምሩ በማድረግ ለዕለቱ ትምህርት መንደርደሪያ ይሆናል፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ሀገር በቀል የሙዚቃ ጫወታዎችን እውቅናና አድናቆት መስጠት ማለት ልጆች የራሳቸውን (የአካባቢያቸውን) ባህልና ወግ በማወቅ የሙዚቃ ጫወታዎችን በመጫወት ለማያውቁት በማሳወቅ የሀገራቸውን የሙዚቃ ጫዎታዎች እውቅናንና አድናቆትን እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ለምሳሌ በአዲስ አመት ወቅት ወንዶች ልጆች የቡሄን ጨዋታ ሲጫወቱ ሴቶች ደግሞ አበባ አየሽ ወይ እያሉ በመዘመር በዓሉን ያከብራሉ፡፡



ምስል 4.3 በሴቶች የሚዘመር የአበባየሽ ሆይ ምስል



ምስል 4.4- በወንዶች ዘንድ የሚዘመር የሆያ ሆዬ ምስል

**መልመጃ 4.9**

- በአካባቢያችሁ በዘመን መለወጫ እና በበዓላት ወቅት የሚዘመሩ መዝሙሮችን በግልም ሆነ በቡድን በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች የተለማመዱትን መዝሙሮች ከበሮ፣ ዲንኬ፣ ፊላ፣ እና ሌሎች በአካባቢያቸው በሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዲያቀርቡ እገዛ ያድርጉላቸው

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ሃገረሰባዊ እውቀቶችን ያያሉ ያደንቃሉ። በተጨማሪም ተማሪዎች ስዕልን ፣ ሙዚቃን ፣ ትያትርን እና ስነ-ጽሁፍን ደጋግመው ሲለማመዱ የሚያገኙትን ጥቅም በስፍት ተመልክተናል። በዋናነት ተማሪዎችን እናድን ነገር ደጋግመ በመለማመዳቸው የሚያገኙትን ጥቅም በዝርዝር ተወያይተናል። በመጨረሻም ተማሪዎች እምቅ ችሎታቸውን አውጥተው ለመጠቀም ብዙ ጊዜ መለማመድ ይገባቸዋል።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶችን ዘርዝሩ
2. በአካባቢያችሁ በበዓላት ወቅት የሚዘመሩ መዝሙሮችን ዘርዝሩ
3. በቤታችሁ የተለያዩ ፎቶዎችን በማንሳት ተለማመዱ
4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ዘርዝሩ
5. ትያትርን ወይም ድራማን ደጋግሞ መለማመድ የሚያስገኘውን ጥቅም ዘርዝሩ

## ፍንጭ

1. በሚኖሩበት አካባቢ የሚገኙ የቤት አሰራር አይነቶችን ይዘረዝራሉ
2. የአዲስ አመት መዝሙሮች እንደየ ባህሉ የተለያዩ ናቸው። ስለሆነም መምህሩ ተማሪዎችን በሚኖሩበት አካባኢ ያሉ ማህበረሰባዊ ዜማዎችን እንዲዘረዝሩ ያደርጋል።
3. በዚህ ርዕስ ተማሪዎች የግል ችሎታቸውን ለማዳበር የተለያዩ ፎቶዎችን በካሜራ ወይም በተንቀሳቃሽ ስልክ በማንሳት ይለማመዳሉ
4. መምህሩ ተማሪዎች በሚሮሩበት አካባቢ የሚገኙ ታሪካዊ እና ባህላዊ ነገሮችን በምሳሌነት በመጥቀስ ለተማሪዎች ያስረዳል
5. ትያትርን ደጋግመን ስንለማመድ ፣ በራስ መተማመናችንን ይጨምራል ፣ ድራማው በአዕምሯችን ውስጥ ለረጅም ዘመናት ይቆያል... ወዘተ

ምዕራፍ አምስት

# 5.የትውን እና እይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማዛመድ

ለምዕራፉ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 23

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የእይታና የትውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ዝመድና በስፋት እንመለከታለን:: በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የእይታና የትውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ከፍተኛ ዝምድና አለው:: የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን ከሒሳብ እና ማህበረሰባዊ ሳይንስ ጋር በማዛመድ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ ለማስቻል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: የተለያዩ መዝሙሮችን አካባቢን ከማስዋብ እና ከማጽዳት ጋር በማያያዝ እንዲዘምሩ በማድረግ የተማሪዎችን አስተሳሰብ ሰፋ ለማድረግ ያግዛል::

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኂላ

- የዕይታና የትውን ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች እንዲሁም ከእርስ በርሳቸው ጋር ያዛምዳሉ
- የተፈጥሮ ቀለማትን በመመልከት መዝሙሮችን እና ውዝዋዜዎችን ያዘጋጃሉ
- ዝርግ ቅርፆችን ከሒሳብ ትምህርት ጋር ያዛምዳሉ
- አካባቢን በማስዎብ እና የግል ንጽህናን በመጠበቅ ላይ መሰረት ያደረጉ ዝማሬዎችን ይዘምራሉ

**ለምዕራፉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- የመለማመጃ አዳራሽ/ክፍል
- አካባቢያዊ የሆኑ የድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫዎቻዎችን ፣ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች … ወዘተ
- የድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል መሳሪያዎች
- እርሳስ፤ ባለቀላም ጠመኔ (ክራዮን) እና ሌሎች በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የእይታ ጥበብን ከሒሳብ ትምህርት ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ
- ሰለ ንጽህና እና አካባቢን ስለመንከባከብ መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ያድርጉ
- ዝርግ ቅርፃችን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያዛምዱ

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ከሌሎች የትምህርት አይነት ጋር የተዛመዱ ስዕሎችን በመስራት
- በቡድን እና በግል ለተለያዩ የትምህርት አይነቶች መርጃ መሳርያ የሚሆኑ የፈጠራ ስራዎችን ሲሰሩ በማይትና በመገምገም
- ገለፃ እንዲያደርጉ በማድረግ

## 5.1. የአይታና የትውን ጥበባት እርስ በርስ ያላቸው ዝምድና

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 4

*መግቢያ*

በዚህ የትምህርት ክፍለጊዜ የእይታና የትውን ጥበባት ማለትም ሥዕል፣ ሙዚቃ ፣ ትያትር እንዲሁም ዳንስ ያላቸውን ዝምድና ይመለከታሉ፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ተማሪዎች በሥዕል፣ በሙዚቃ፣ በትያትር እንዲሁም በዳንስ መካከል ያለውን ዝምድና ያጠናሉ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች በሥዕል፣ በሙዚቃ፣ እንዲሁም በትያትር መካከል ያለውን ልዩነት ተናገሩ

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎችን ከዚህ ቀደም የነበራቸውን ግንዛቤ በመለካት ወደ ትምህርቱ ለመሄድ መንደርደሪያ ያድርጉ

### 5.1.1. ሥዕል ፤ሙዚቃ፤ እና ትያትር ያላቸው ዝምድና

በመሰረታዊነት ሥዕል ፤ሙዚቃ፤ ትያትር እንዲሁም ዳንስን ለመነጣጠል የሚከብዱ ብዙ ዝምድናዎች አላቸው፡፡ ለምሳሌ የትያትር፣ የሙዚቃ እና የሥዕል መሰረትዊ አላባውያን ተቀራራቢ የሆነ የሃሳብ ግንኙኙነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ቀለም፣ ውበት፣ ልዩነት ወዘት የመሳሰሉ ነገሮች በትያትር፣ በሙዚቃ እና በሥዕል ውስጥ የምናገኛቸው መሰረታዊ ሃሳቦች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት አብዛኞቹ የእይታና የትውን ጥበብ ሃሳቦች የሚወራረሱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

አንድን የመድረክ ትያትር ብንመለከት ሥዕል ፣ ሙዚቃን እና ዳንስን በአንድላይ የያዘ ነው፡፡ አንድ ትያትር ለተመልካች ከመቅረቡ በፊት የሚቀርብበት መድረክ በትክክል ከትያትሩ ጋር እንዲዛመድ ተደርጎ ዲዛይኑ ይሰራል፡፡ ይህ የመድረክ ዲዛይን በአብዛኛው በሰዓሊ የሚሰራ ሲሆን በሥዕል፣ በቅርፃ-ቅርፅ፣ እንዲሁም

የተለያዩ አልባሳትን እና ቁሳቁሶችን ሰዓሊው በማዘጋጀት መድረኩ ለተመልካቾች ውብ እና ማራኪ ሆኖ እንዲታይ ያደርጋል:: በመቀጠል ሙዚቀኛው ደግሞ ከትያትሩ ጋር አብረው የሚሄዱ ሙዚቃዎችን በማዘጋጀት ትያትሩ በሚሰረበት ጊዜ ከመድረክ ጀርባ በመሆን ሙዚቃ መሳሪያዎችን ሊጫወት ይችላል ወይም በድምጽ ሊያዜም ይችላል:: በሶስተኛ ደረጅ በአንድ ትያትር ውስጥ ዳንስ ወይም ውዝዋዜ ይኖራል:: በዚህ ወቅት ትያትሩን የሚሰሩ ሰዎች ሊወዛወዙ ወይም ሊድንሱ ይችላሉ:: በአጠቃላይ በአንድ ትያትር ውስጥ የእይታ እና የትውን ጥበባት እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው የሚሄዱ የትምህርት አይነቶች እንደሆኑ ማሳየት እንችላለን::

## 5.2. የእይታና የትውን ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማገናኘት መግቢያ

በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን እና ቅርፆችን ከሂሳብ እና ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማዛመድ እንድንማር ለማድረግ ነው::

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- ዝርግ ቅርፆች ከስዕል እና ከሒሳብ ትምህርት ጋር ያላቸውን ዝምድና ይረዳሉ
- ቅርፆች ሒሳብን ለመማር ያላቸውን ጠቀሜታ ይረዳሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ወረቀት
- እርሳስ
- እስክርቢቶ

- ባለቀለም ክራዩን/ማርከር

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ዝርግ ቅርፆችን ከሒሳብ ትምህርት ጋር እያዛመዱ እንዲስሉ ያድርጉ
- ጂኦሞአትሪያዊ ዝርግ ቅርፆችን ከሒሳብ ትምህርት ጋር እያዛመዱ ሥዕል ይሳሉ

**የግምገማ እና ክትትል ስልት**

- የተሰሩ ቅፆችን በመመልከት
- ጥያቄ ዎችን በመጠየቅ እንዲመልሱ በማድረግ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት በሒሳብ መጽሃፍ ላይ ተስለው ያያችኋቸው ዝርግ ቅርፆች ዘርዝሩ፡፡

**ፍንጭ**

- በዚህ ጥያቄ መምህሩ በተለያዩ መጽሃፍት ውስጥ ተስለው የሚገኙ ዝርግ ቅርፆችን እንዲያስታውሱና በስዕል እና በሒሳብ መካከል ያለውን ልዩነት ያደርጋሉ፡፡

## 5.2.1. ዝርግ ቅርፆችን ፣ ቅርፆችን እና ቀለማትን ከሒሳብና ሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማዛመድ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 2

### ጠቃሚ መረጃ

ስለ ዝርግ ቅርፆች እና ቅርፆች ባህሪያት በምዕራፍ አንድ ላይ በስፋት ተምረዋል፡፡ በሒሳብ ትምህርት ውስጥ የሚገኘው ጂኦሜትሪ የሚያጠናው ስለዝርግ ቅርፅ እና ቅርፅ ሲሆን ስፋት ፣ ይዘት ፣ ዲያሜትር  እንዲሁም ሬድየሱን ምን ያክል እንደሆን በቁጥር ይገልጣል፡፡ ስነ-ጥበብና ሒሳብ የቆየ ዝምድና አላቸው፡፡ ከጥንታዊ የዋሻ ግድግዳ ላይ ስዕሎች ጀምሮ ጂአኦሜትሪያዊ ዝርግ ቅርፆችን በተለያየ መንገድ ያሳዩ ነበር፡፡ በተጨማሪም ክፍልፋዮችን በስዕል ውስጥ ለማስቀመጥ እና ለማመጣጠን ሂሳባዊ ስሌቶችን ተጠቅመዋል፡፡ ለዚህም ወርቃማ አወቃቀር (golden proportion) የምንለው በአንድ የመሳያ ወረቀት ወይም ግድግዳ ላይ እንዴት መቀመጥ አለበት የሚለውን የምናስቀምጥበት ቦታ ነው፡፡ ጂኦሜትሪያዊ ቅርፆች ልክ እንደ ስዕል የሚጀምሩት ከነጥብ ወደ መስመር እንዲሁም ወደ ቅርጽ ያድጋል፡፡ ጂኦሜትሪ ከስዕል በተጨማሪ ለኪነ-ህንፃ ትልቅ መነሻ ነው፡፡ በአካባቢያችን አብዛኛዎቹ ህንፃዎች የተለያዩ ሰው ሰራሽ ቅርፆችን በመገጣጠም የሚሰሩ ናቸው፡፡  ዝርግ ቅርፆች እና ቅርፆች በሒሳብ ክፍት እና ዝግ ተብለው ይጠራሉ፡፡ በስዕል ዝርግ ቅርጽ የምንለው ሁልጊዜ ዝግ ሲሆን (የአንድ መስመር ሁለት ጫፎች ሲገናኙ) ነው፡፡

የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችን ወደ ባር ግራፍ ለመለወጥ የተለያዩ አይነት ቅርፆችን እና ዝርግ ቅርፆችን መጠቀም እንችለላልን፡፡ ስዕላዊ ዲያግራሞች በዋናነት የምንጠቀመው ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህሩ በቀላሉ ለመግባባት እንዲያግዛቸው ለማድረግ ነው፡፡ መምህሩም የተለያዩ ሃሳቦችን በማንሳት በክፍል ውስጥ ያሳዩ፡፡

በተማሪዎች መጽሃፍ ላይ በዚህ ትምህርት ውስጥ የተካተቱትን ዲያግራሞች መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ከሒሳብ ትምህርት በተጨማሪ የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን በመገጣጠም ዲዛይኖችን እንዲሰሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ መምህሩም ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች በመፍጠር ለተማሪዎች እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

**መልመጃ 5.1**

- ተማሪዎች በሒሳብ ትምህርት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን በመጠቀም ዲዛይኖችን ስሩ፡፡

**ፍንጭ**

- መምህሩ በጥያቄው መሰረት የተለያዩ ሰውሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርፆችን (ሶስት ጎን ፣ አራት ጎን ፣ ትራፒዝየም…ወዘተ) በመጠቀም ዲዛይኖችን እንዲሰሩ መምህሩ እገዛ ያድርግላቸው፡፡

## 5.2.2. ስነ ጥበብ ከአካባቢ ሳይንስ ትምህርት እና ቀለማትጋር ያላቸው ዝምድና

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 3

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ካርቶን
- ወረቀት
- ቀለም
- ኮላ/ሙጫ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የተለያዩ ሀገሮችን ካርታ እየሳሉ ተፈጥሯዊ ዝርግ ቅርፆችን ይለማመዱ

- የሚስሉትን ሥዕል በመመልከት ክትትል ያድርጉ
- የሰሩት ሥዕል ትክክል መሆኑን በማየት ገንቢ አስተያየት ይስጡ

**የግምገማ እና ክትትል ስልት**

- ለማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት የሚያገለግሉ የመርጃ መሳሪያዎችን ሲሰሩ በማየት
- ስነ ጥበብ ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ያለውን ዝምድና ሲሰሩ በማየት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ካርታዎችን በየትኛው የትምህርት አይነት ላይ ተስለው እንደተመለከታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ::

**ፍንጭ**

- በዚህ ርዕስ የተለያዩ አይነት ካርታዎችን የት እንደተመለከቱ ሲናገሩ የትምህርት አይነቶችን ከስዕሎች ጋር እንዲያገናኙ ለማድረግ ነው::

**ጠቃሚ መረጃ**

ስነ-ጥበብ ከማህበረሰባዊ ትምህርቶች ጋር ሰፊ ዝምድና አለው:: ማህበራዊ ሳይንስ የምንላቸው ታሪክ ተፈጥሯዊ ገፅታን ፣ ታሪከ እንዲሁም የሰዎችን ባህል እና የአኗኗር ሁኔታ ስዕላዊ በሆነ መንገድ ለማሳየት ይጠቅማል:: የእይታ ጥበባት የተለያዩ ካርታዎችን ፣ በትንንሽ መጠን የተሰሩ ማሳያ ቅርጽ (ተምሳሌቶች) እንዲሁም ቻርቶችን ለመስራት ይጠቅማል:: ለምሳሌ የብዙ አፍሪካ ሃገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ የሃገራት ካርታዎች የተሸራረፉ የሚመስሉ (ተፈጥሯዊ)

ቅርፆች ናቸው፡፡ ስለዚህ ስለተፈጥሯዊ ቅርፆች ለመማር የተላያዩ ሀገራትን ቅርፅ ማየት በቂ ነው፡፡




ምስል 5.1- የአፍሪካ ካርታ



ምስል 5.2- የኢትዮጵያ ካርታ

ለምሳሌ ዝናብ እንዴት እንደሚፈጠር ለማሳየት መጀመሪያ የፀሀይ ሙቀት ከተለያዩ የውሃማ አካላት ላይ (ወንዝ ፣ ኩሬ ፣ ሃይቅ ፣ ውቅያኖስ) ሲያርፍ እና በትነት መልኩ እንዴት ወደ ደመና እንደሚቀየር እናሳያለን። ቀጥሎ በትነት መልክ የተሰበሰበው ደመና ቅዝቃዜን በምፍጠር ቀስ በቀስ ወደ ዝናብ ነጠብጣቦች ይቀየራል ማለት ነው። ይህንንም በስዕል መልክ እንደሚከተለው ልናሳየው እንችላለን ማለት ነው።



ምስል 5.3- የዝናብን አፈጣጠርና ኡደት የሚያሳይ ቻርት

**መልመጃ 5.2**

- ከላይ በምስሎች የተመለከትነውን መሰረት በማድረግ ሌሎች ለተፈጥሮ ሳይንስ መርጃ መሳሪያ ሊሆኑ የሚችሉ ስዕሎችን እና ዲያግራሞችን ስሩ፡፡

**ፍንጭ**

- በተሰጠው ጥያቄ መሰረት ተማሪዎችን ከህብረተሰብ ትምህርት ጋር ተያያዥ የሆኑ የታሪክ እንዲሁም የተፈጥሯዊ መልከዓ-ምድርን የሚያሳዩ ነገሮችን በወረቀት ፣ በካርቶን ፣ በጭቃ እንዲሁም በጨርቅ በመስራት ማብራሪያ እንዲያደርጉ ማድረግ ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡

### 5.2.3. የእይታ ጥበብ ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ዝምድና

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 2

የተፈጥሮ ሳይንስ የምንላቸው የትምህርት አይነቶች ስለ ንጥረ ነገሮች ፣ ስለ ቁሳቁሶች ባህሪ እና የእንቅስቃሴ ሁኔታ ፣ እንዲሁም ስለ አከባቢ የአየር ጸባይ ሁኔታዎች እና ባህሪያቸውን የሚያጠና ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ርዕስ ተፈጥሯዊ ነገሮችን ከዕይታ ጥበብ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት እናጠናለን፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ

- የዕይታ ጥበብ ከሳይንስ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና ይረዳሉ
- ለሳይንስ ትምህርት የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳያሉ
- አዳዲስ ቀላል ነገሮችን ለመስራት ይችላሉ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የእይታ ጥበብ ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ዝምድና እንዲናገሩ እድል ይስጡ
- ከተማሪዎች ምላሽ በመነሳት ማብራሪያ ይስጡ
- ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄ በመጠየቅ እንዲመልሱ ያድርጉ
- በመጨረሻም የእይታ ጥበብ ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ዝምድና ያጠቃሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ለተፈጥሮ ሳይንስ መርጃ መሳሪያ የሚያገለግሉ በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶች
- ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች
- ማጣበበቂያ
- ጨርቆች
- ቀለም
- ማርከር

**የግምገማ እና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎች የሰሩትን በመመልከት ስለሰሩት ነገር ማብራሪያ እንዲሰጡ በማድረግ

**ጠቃሚ መረጃ**

ጥበብ ሳይንስ ነው ወይም ሳይንስ ጥበብ ነው ስንል በመመራመር አዲስ ነገሮችን የምናገኝበት መንገድ ስለሆነ ነው:: ስለዚህ የሳይንስ እና የእይታ ጥበብን ነጣጥሎ ማየት ስለሚከብድ ነው:: አንድ የፈጠራ ስራ በተግባር ከመሰራቱ በፊት ስዕላዊ በሆነ መንገድ ይቀመጣል:: ለምሳሌ አውሮፕላን በተግባር ተሰርቶ ከመብረሩ በፊት አጠቃላይ ውጫዊ እና ውስጣዊ ገጽታው በስዕል ከተቀመጠ በኋላ ቀጣዩ የአውሮፕላን ክፍል መገጣጠም ይጀመራል ማለት ነው:: ለምሳሌ አውሮፕላን የመስራት ጽንሰ-ሃሳብ የተጀመረው በአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት (ከዛሬ ስድስት መቶ አመታት በፊት) በጣልያናዊው ሰዓሊ ሊኦናርዶ ዳቬንቺ ሲሆን በተግባር የተሰራው ደግሞ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ (ከዛሬ መቶ አስራ አምስት አመታት በፊት) በሁለት ወንድማማቾች ዊልቨር ራይት እና ኦሊቨር

ራይት አማካኝነት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ስነ ጥበብ ከሳይንስ ጋር ከፍተኛ ግንኙነት እንዳለው መረዳት እንችላለን፡፡

**መልመጃ 5.3**

- ለተፈጥሮ ሳይንስ መማሪያ እና ማስተማሪያ የሚያገለግሉ የተለያዩ ስዕሎችን በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- በዚህ ርዕስ ስር መምህሩ ስለ ቀላል ማሽኖች ፣ ተንቀሳቃሽ ቀላል መኪኖች እንዲሁም ቁሳቁሶችን ተማሪዎች ከአካባቢያቸው በሚያገኟቸው ቁሳቁሶች እንዲሰሩ መመሪያ ይሰጣቸዋል፡፡

## 5.2.3. የትውን ጥበባት ከሌሎች ይትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 4

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ለሚሰሩት ተውኔት/ድራማ አስፈላጊ የሆኑ አልባሳት
- የመለማመጃ ክፍል
- ከድራማው ጋር ተያያዥ የሆኑ ታሪካዊ ፎቶዎች እና ተንቀሳቃሽ ምስሎች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የትውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለሌሎች ተማሪዎች ይናገሩ
- የተወያዩትን ሀሳብ መምህሩ ያጠቃሉ

## የግምገማ እና ክትትል ስልት

- የሰበሰቧቸውን አልባሳት እና ያቀረቡትን ተውኔት በመመልከት
- ያቀረቡት ተኔት የሚያስተለልፈውን ታሪካዊ መልዕክት በመገምገም

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

> ➢ በአካባቢያችሁ አንድን ማህበረሰብ ለማበረታታት ወይም ለመቃወም የሚነገሩ እና ድራማ ሊሰራባቸው የሚችሉ ሃሳቦች ካሉ ለመምህራችሁ ተናገሩ::

## ጠቃሚ መረጃ

የትወና ጥበብ ከታሪክ ጋር ትልቅ ግንኙነት አላቸው:: ታሪካዊ ክንውኖችን ለተመልካቾች በሚመች መልኩ የተለያዩ አልባሳቶችን በመጠቀም ማሳየት እንችላለን:: ለምሳሌ የነገስታቶችን ታሪክ ማለትም የወላይታን ንጉስ ካዎ ጦናን ፣ የሲዳማን ንግስት ፉራን ፣ የኮንሶን ጎሳ መሪ ቦቆላን የዳውሮን ንጉስ ካኦ ሃላላን … ወዘተ ታሪክ በመውሰድ በትያትር እና በድራማ መልኩ ብናቀርብ ተመልካቾች ከመዝናናት በተጨማሪ ታሪክም ያውቃሉ:: ስለ ነገስታት ድራማ ስንሰራ ትክክለኛው አልባሳት ምን ይመስል እንደነበርና ምን አይነት እንቅስቃሴዎችን ያሳዩ እንደነበር ለማስረዳት ያግዛል:: ለምሳሌ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ፓንቶ ማይምን በመጠቀም ያለ ንግግር የነገስታቶችን የሰውነት እንቅስቃሴ እና የአለባበስ ሁኔታ ማሳየት ይቻላል:: ቀደምት አባት አርበኞቻችንን እንቅስቃሴ እና አልባሳቶችን በመልበስ መከወን አንዱ መንገድ ነው::

ተውኔቶች የራስችንን እምቅ ችሎታ ከማሳደግ በተጨማሪ ማህብራዊ መስተጋብርንም ያሳድጋል፡፡ በአንድ ድራማ ሁላት እና ከዚያ በላይ ሰዎች ሊሳተፉበት ይችላሉ፡፡ ከብዙ ሰዎች ጋር አብረን በሰራን ቁጥር ከሰዎች ጋር መግባባትን ፣ አብሮ መስራትንና ተሳትፎን ይጨምራል፡፡ ስለዚህ ከተለያዩ ሰዎች ወይም ተማሪዎች ጋር ድራማም ሆነ ትያትር ስንሰራ አዳዲስ እውቀትን እና ልምድን እንቀስማለን፡፡

የትውን ጥበባት ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ዝምድና ስንመለከት ከህክምና ፣ ከኢንጂነሪንግ እንዲሁም ፊዚክስ ትምህርቶች ጋር በማገናኘት መስራት እንችላለን፡፡ ትያትር የገሃዱ አለም ነጸብራቅ መበሆኑ ለተመልካች በሚመጥን መልኩ አሳምሮ ማቅረብ ነው፡፡ አንድ ድራማ ውስጥ የሒሳብ መምህር ገጸ-ባህሪ ቢኖር እርሱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በማጥናት ተውኔቱ ይሰራል ማለት ነው፡፡ የቃላት አጠቃቀም ፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ፣ የእጅ ጽሁፍን እንዲሁም ሌሎች ባህሪያትን በትክክል ለተመልካች ለማሳየት ይጠቅማል፡፡

**መልመጃ 5.4**

- ተማሪዎች ከአካበያቸው የሚያውቁትን ታሪካዊ እና ባህላዊ ክንዋኔዎችን በመውሰድ በቡድን በቡድን በምሆን ተውኔት/ድራማ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

**ፍንጭ**

- በተሰጠው ጥያቄ መሰረት መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የተላዩ ርዕሶችን ለተማሪዎች ከፋፍሎ ይሰጣል፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕስ መሰረት የተለያዩ ገፀ-ባህሪያትን ተለማምምደው እንዲጫወቱ መምህሩ እገዛ ያድርግላቸው፡፡

### 5.2.4. ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 5

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት በነበሩ የሙዚቃ ትምህርቶቻችሁ ላይ ስለተለያዩ የትምህርት አይነቶች የዘመራችኋቸውን መዝሙሮች በማስታወስ በዜማም ሆነ በግጥም ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ፍንጭ**

- መምህሩ ተማሪዎችን ከዚህ በፊት በሙዚቃ ትምህርታቸው ስለዘምሯቸው መዝሙሮች እንዲያስታውሱ ያግዛቸዋል። በመቀጠል አንድ ጊዜ በህብረት ከዘመሩ በኋላ ወደ እለቱ ትምህርት ያልፋል።

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ተማሪዎችን ከዚህ በፊት ስለተማሯቸው መዝሙሮች እንዲዘምሩ ያድርጉ
- ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ
- የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጡ

**የግምገማ እና ክትትል ስልት**

- ተማሪዎች ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጋር ሙዚቃን እያዛመዱ የሚያቀርቧቸውን መዝሙሮች በማዳመጥ ውጤት መስጠት

**ጠቃሚ መረጃ**

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች ሙዚቃ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ዝምድና ትማራላችሁ። ስለዚህ ሙዚቃ ከሒሳብ ፣ ከተፈጥሮ ሳይንስ እንዲሁም ከህብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት እና ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን ዝምድና ከዜማ እና ከውዝዋዜ ጋር በማዋሃድ ትከውናላችሁ።

**ሀ. ሙዚቃ ከሒሳብ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና**

ሙዚቃን ከሒሳብ ትምህርት ጋር በማገናኘት ስለ ቁጥሮች እና መሰረታዊ የሒሳብ ስሌቶችን ማስተማር እንችላለን። ለምሳሌ ሙዚቃ ከሒሳብ ትምህርት ጋር ስናገናኘው ስለመደመር ፣ መቀነስ ፣ ማባዛት ፣ ማካፈል ሙዚቃን ልንጠቀመው እንችላለን።

**ጠቃሚ መረጃ**

ሙዚቃ የአለም ቋንቋ ነው ስንል ያለ ምክንያት አይደለም። ሙዚቃ አብዛኛውን የአለማችንን ክፍል ያግባባል ያስደስታል እንዲሁም ስሜት ለመግለጽ ያግዛል። በተመሳሳይ የሙዚቃ ትምህርትን ከሁሉም የትምህርት አይነቶች ጋር በማገናኘት ለህፃናት ማስተማሪያ አይነተኛ መንገድ ነው። ሙዚቃን እንደ ማህደረ ትውስታ መጠቀም ጠቃሚ የማስተማሪያ መንገድ ሊሆን ይችላል ለምሳሌ ስለሒሳብ ፣ ስነህይወት ፣ ስነምግባር ፣ ስፖርት ፣ አከባቢ ሳይንስ ወ.ዘ.ተ ያካትታል።

**ምሳሌ፡-**

ይህ በስታፍ የተፃፈው መዝሙር አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ የሚለው ሲሆን መምህሩ በዚህ ዜማ ማሰረት ለተማሪዎች እንዲዘምሩ እና እንዲለማመዱ ያደርጋል።

## አምስት አረንጓዴ ጠርሙሶች

አምስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ

ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አራት ይቀራል

አራት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ

ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሦስት ይቀራል

ሦስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ

ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሁለት ይቀራል

ሁለት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ

ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አንድ ይቀራል

አንድ አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ

ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ዜሮ ይቀራል




**ምስል 5.4- አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች መዝሙር**

## መልመጃ 5.5

- ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው

ፍንጭ

- መምህር እባክዎች ተማሪዎች ስለተለያዩ የትምህርት አይነቶች የተዘመሩ መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ድጋፍ ያድርጉላቸው

### ለ. ሙዚቃን ከሳይንስ ትምህርት ጋር በማገናኘት መዘመር

### ጠቃሚ መረጃ

ሙዚቃን ከግልና ከአከባቢ ንፅህና ጋር በማዛመድ የግልና የአከባቢያችንን ንፅህና እንዴትና በምን ሁኔታ መጠበቅ እንዳለብን፣ ስለእርሻ በሙዚቃ እንማራለን፣ ሙዚቃን ከተፈጥሮ ጋር በማዛመድ ስለተፈተፈጥሮ በመዘመር በሚግባ ልንረዳው እንችላለን ሙዚቃን ከተለያዩ እንስሳትን አዕዋፋት ጋር በማዛመድ፣ በሙዚቃ ስለ ሀገር ፍቅር፣ ስለቤተሰብ ፍቅር በሚገባ ልንማር እንችላለን፡፡ በአጠቃላይ በሙዚቃ ስለተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዛመድ እንማራለን፡፡

### ሳይንስ ሳይንስ

ሳይንስ ሳይንስ መዳኒቴ

ያስተማረኝ ጤንነቴን

ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን ስበላ

ለትምህርት ስሄድ ሳይንስ ላጠና

እጄን ታጥቤ ምሳ ስበላ

ደግሞ ይታየኛል የሳይንስ መላ

እግሬን ታጥቤ ማታ ስተኛ

በህልሜ ታየኝ ሳይንስ ሳጠና

ሙዚቃን ከግልና ከአከባቢ ንፅህና ጋር በማዛመድ የግልና የአከባቢያችንን ንፅህና እንዴትና በምን ሁኔታ መጠበቅ እንዳለብን ይስተምራል፡፡ ስለ እርሻ  እንዲሁም ከተለያዩ እንስሳትና አዕዋፋት ጋር በማዛመድ ልንዘምር እንችላለን፡፡ ሙዚቃን ስለ ሀገር ፍቅርና ስለ ቤተሰብ ፍቅር የተለያዩ ዜማዎችን በመጠቀም ሃሳባችን ልንገልጽ  እንችላለን፡፡

ሙዝዚቃን ከስፖርት ሳይንስ ጋር በማዛመድ የተለያዩ መዝሙሮችን መዘምር እንችላለን፡፡

ለምሳሌ፦

**መዝሙር፦ 5.3**

ስፖርት መስራት ለጤንነት

ስፖርት መስራት ለጤንነት

እንሩጥ ሩጫ ሩጫ ሩጫ

እንዝለል ዝላይ ዝላይ ዝላይ

**መዝሙር 5.4**

ይስተምራል፡፡ስለ እርሻ  እንዲሁም ከተለያዩ እንስሳትና አዕዋፋት ጋር በማዛመድ ልንዘምር እንችላለን፡፡ ሙዚቃን ስለ ሀገር ፍቅርና ስለ ቤተሰብ ፍቅር የተለያዩ ዜማዎችን በመጠቀም ሃሳባችን ልንገልጽ  እንችላለን፡፡

## እፅዋት እተክላለሁ

X2 እኔስ በግቢዬ በስፈሬ በሰፈሬ
እፅዋት እተክላለሁ አሳምሬ አሳምሬ

አረንጓዴ ተክል ቢጫ ቀለማት
ቀይ ነው አበባ ደማቅ ለውበት
ለማስዋብ ግቢዬን ይኽነው ምርጫዬ
ደግምም በሰፈሬ የኔ አበባዬ

X2
ኦኔስ በግቢዩ በሰፈሬ በሰፈሬ
እፅዋት እተክላለሁ አሳምሬ አሳምሬ

ደስታ ይሰማኛል ውሃ ሳጠጣሽ
የምከባከብሽ የኔ ምርጫ ነሽ
ውበትሽ ግሩም ነው ቀለመ ደማቅ
እመራመራለሁ አንቺን ለማወቅ

X2 እኔስ በግቢዬ በስፈሬ በሰፈሬ
እፅዋት እተክላለሁ አሳምሬ አሳምሬ




ምስል 5.5- ሰለ እፅዋት የተዘመረ መዝሙር

**መልመጃ 5.6**

- ተማሪዎች የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚዘመሩ መዝሙሮችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡላቸው::

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች መዝሙሮችን እንዲያቀርቡ እገዛ አርጉላቸው::

## ሐ. ተማሪዎች በየቀኑ የሚያደጓቸውን ድርጊቶች በመዝሙር መግለጽ

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 2

የሰው ልጆች በተለምዶ ማንኛውንም ስራ በሚሰሩበት ወቅት እንቅስቃሴ በማድረግ እና መዝሙሮችን በመዘመር(ሙዚቃ በማዳመጥ) የትኛውንም ዓይነት ስራን ሊከውኑ ይችላሉ ከእነዚህም ስራዎች መሃል ለአብነት ያህል ፊታቸውን ሲታጠቡ መዝሙሮችን ይዘምራሉ የቤታቸውን፣ የአካባቢያቸውን፣ የመስሪያ ቤታቸውን ቁሳቁሶች ሲያፀዷቸው መዝሙሮችን በመዘመር ይከውኑታል በተጨማሪም አካባቢያቸውን ሲያፀዱም መዝሙሮችን እየዘመሩ ያፀዱታል ይህንንም የሚያደርጉት የሚሰሩትን ስራ ስለሚያፈጥንላቸው ወይም አእምሯቸውን ነፃ አድርገው ስራቸውን ለመከወን ሲፈልጉ ነው፡፡

### ከርዕሱየሚጠበቁውጤቶች

- ተማሪዎች በቤታቸውና በአካባቢያቸው ስራን በሚሰሩበት ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይረዳሉ

### የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ስለ ጽዳት የተዘመዱ መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ያድርጉ
- ተጨማሪ ዜማዎች ካሉ ይዘምሩ

### የግምገማ እና ክትትል ስልት

- ተምሪዎች መዝሙሮችን ሲያቀርቡ በማዳመጥ ውጤት መስጠት

**ማነቃቂያ**

- በቤታችሁ ስራን በምትሰሩበት ወቅት ምን በማድረግን ስትሰሩ ያስደስታችኋል።

**ፍንጭ**

- መዝሙር ሲዘምሩ ፣ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ፣ ሲወዛወዙ ወይም ሲዘፍኑ ሊሆን ይችላል።

## ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

ፊታችን እንታጠብ እንታጠብ እንታጠብ

ፊታችን እንታጠብ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

ጥርሳችን እንቦርሽ እንቦርሽ እንቦርሽ

ጥርሳችን እንቦርሽ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

ፀጉራችንን  እናበጥር እናበጥር እናበጥር

ፀጉራችንን እናበጥር ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

ልብሳችንንም እንልበስ እንልበስ እንልበስ

ልብሳችንንም እንልበስ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

ቁርሳችንንም እንብላ እንብላ እንብላ

ቁርሳችንንም እንብላ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

ትምህርት ቤትም እንሂድ እንሂድ እንሂድ

ትምህርት ቤትም እንሂድ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት

**መዝሙር፡-**

አካባቢያችንን ከማጽዳት ጋር በተያያዘ የሚዘመር መዝሙር

**ትምህርት ቤታችን**

2 ጊዜ { ትምህርት ቤታችን በጣም ያማረች
ግቢው የተዋበ ጥሩ የፀዳች

መንገዱ የሚያምር ሳርና ቅጠሉ

በማስዋብ ማሳመር በዚሁ ቀጥሉ

ትምህርት ቤታችን እንከባከብ

ውሃ በማጠጣት ለምልሞ እንዲያብብ

2 ጊዜ { ትምህርት ቤታችን በጣም ያማረች
ግቢው የተዋበ ጥሩ የፀዳች

ለትምህርት ቤታችን እንስራ በጋራ

ለተተኪው ትውልድ አለብን አደራ

ጽዱ እናደርገው ለተክል ቆፍረን

ውሃ በማጠጣት ችግኙን ኮትኩተን

2 ጊዜ { ትምህርት ቤታችን በጣም ያማረች
ግቢው የተዋበ ጥሩ የፀዳች

## ትምህርት ቤታችን




5.6. ትምህርትቤታችን መዝሙር በስታፍ ላይ

**መልመጃ 5.7**

- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚታወቁ ተጨማሪ ስለ ጽዳት የተዘመሩ መዝሙሮች ካሉ  በክፍል ውስጥ ዘምሩ፡፡

**ፍንጭ**

- በጠያቂው መሰረት ተማሪዎች በባህላቸው ውስጥ ስለ ጽዳት የተዘመሩ መዝሙሮች ካሉ እንዲዘምሩ መምህሩ እገዛ ወይም ፍንጭ ይሰጣቸዋል፡፡

### መ. ስለ አካባቢያዊ ቀለማት፣ ዕጽዋትና እንስሳት መዘመር

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 2

መግቢያ

ከዕፅዋትና እንስሳት እንቅስቃሴ የተለያየ አይነት ውዝዋዜዎችን ማስመሰል እንችላለን እፅዋዕቶች ንፋስ ሲነፍስ ወደተለያየ አቅጣጫ ከፍና ዝቅ እንዲሁም ወደጎን ይነፍሳሉ (ይወዛወዛሉ) የተለያዩ አይነት እንስሳቶችም በሚራመዱበት ጊዜ ፣ በሚሮጡበት ጊዜ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያሳዩናል የሰው ልጆችም የዕፅዋቶችንና እንስሳቶች እንቅስቃሴ በመከወን የተለያዩ ውዝዋዜዎችን ማስመሰል ይችላሉ

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከተለያዩ ዕፅዋትና እንስሳት እንቅስቃሴ ውዝዋዜን ይማራሉ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ተማሪዎች ስለ ተፈጥሮ የተዘመሩ መዝሙሮች ካሉ እንዲዘምሩ ያድርጉ
- ስለ እንሣት የተዘመሩ በአካባቢው የሚታወቁ መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ያድርጉ

**ማነቃቂያ**

- የተለያዩ መዝሙሮችን እየዘመራችሁ ከዕፅዋትና እንስሳት እንቅስቃሴ በማስመሰል ውዝዋዜዎችን አስመስሉ፡፡

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች የሚያስመስሏቸውን ውዝዋዜዎችን መመልከትና እገዛ ማድረግ፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ተማሪዎች ከዕፅዋትና እንስሳት እንቅስቃሴ የተለያየ አይነት ውዝዋዜዎችን ማስመሰል እንችላለን እፅዋዕቶች ንፋስ ሲነፍስ ወደተለያየ አቅጣጫ ከፍና ዝቅ እንዲሁም ወደጎን ይነፍሳሉ (ይወዛወዛሉ) የተለያዩ አይነት እንስሳቶችም በሚራመዱበት ጊዜ ፣ በሚሮጡበት ጊዜ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያሳዩናል የሰው ልጆችም የዕፅዋቶችንና እንስሳቶች እንቅስቃሴ በመከወን የተለያዩ ውዝዋዜዎችን ማስመሰል ይችላሉ፡፡

**መልመጃ 5.8**

- ተማሪዎች ስለ ዛፎች ፣ ስለ አበቦች እና ወፎች በባህላቸው የሚታወቁ መዝሙሮችን ከሚዘምሩለት ነገር እንቅስቃሴ ጋር በማዛመድ አሳዩ::

**ፍንጭ**

- ለምሳሌ ስለ ዛፎች ሲዘምሩ ልክ እንደ ዛፎች እየተወዛወዙ ፣ ስለ አዕዋፋት ሲዘምሩ የመብረር እንቅስቃሴ በማድረግ እንዲሁም ስለ ፏፏቴዎች ሲዘምሩ በአፋቸው የፏፏቴውን ድምጽ በማምስመሰል እንዲለማምመዱ ማድረግ::

## 5.2.5. ገጸ-ባህሪያትን መጫወት

ለርዕሱ የተመደበው የክፍለ-ጊዜ ብዛት 3

ገጸ-ባህሪ በአንድ ተውኔት ወይም ድርሰት ውስጥ የሚገኝ የተውኔት ክፍል ነው:: ገጸ-ባህሪ በአንድ ተውኔት ወይም ድራማ ውስጥ ያሉ የሰዎችን ባህሪ የሚያሳዩ ክንዋኔዎች ናቸው:: በአንድ ተውኔት ውስጥ የተለያዩ አይነት ገጸባህሪያት ቢኖሩም በዋናነት ግን ወጥ እና አስተኔ ገጸ-ባህሪያት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ:: ተውኔት በመድረክ ላይ ተመልካቾችን በቀጥታ በማግኘት የሚከውን ጥበብ ነው:: ተውኔት ፣ ፅሁፈ ተውኔት ወይም ድርሰት የተፃፈውን የምናብ ድርሰት ታሪክ ገፀ-ባህሪ እና ድርጊቶችን ጨምሮ ህይወት የምንዘራበት ሂደት ነው:: ተውኔት በመድረክ ላይ ወደ አፈፃፀም የሚቀየር የስድ ወይም የግጥም ጥንቅር ነው:: ታሪኩ በባህሪያቱ መካከል ባለው መስተጋብር የሚገፋ እና ለተመልካች

በመልእክት በትግበራ የሚበቃ ነዉ። ተውኔት በንግግር ውይይት ላይ በእጅጉ የተመረኮዘ ነው።

**መልመጃ 5.9**

- ተማሪዎች የተለያዩ ወጥ-ገጸባህሪያትን እና አስተኔያዊ ገጸ-ባህሪያትን በመላበስ ተጫወቱ

**ፍንጭ**

- መምህር እባክዎ የተለያዩ አይነት ገጸ-ባህሪያትን ለተማሪዎች በማከፋፈልና እንዲለማመዱ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የእይታ እና የትውን ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ዝምድና በሰፊው ተመልክተናል። ስዕል ፣ ሙዚቃ እና ተውኔት ከትምህርቱ በተጫማሪ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በማያያዝ የፈጠራ እና የማመዛዘን ችሎታን ለመጨማር ያግዛል። ለምሳሌ ስዕል የተለያዩ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ለመስራት ፣ ካርታዎችን ለማዘጋጀት እንዲሁም ታሮካዊ ክንዋሌዎችን በፎቶ እንዲሁም በተንቀሳቃሽ ምስል መልክ ለማሳየት ያግዛል። መዝሙሮችን በመጠቀም ሒሳብን ፣ ሳይንስን እና አካባቢን ለምጠበቅ የሚያግዙ እንቅስቃሴዎችን ማስተለለፍ እንችላለን ማለት ነው። የትውን ጥበባት የሚባሉት ድራማ እና ተውኔቶችም እንዲሁ የተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮችን በማንሳት ለማህበረሰቡ በቀላሉ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በአጠቃላይ የትውን እና የእይታ ጥበባት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ ክንዋኔዎችን አጭር እና ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ያዛሉ።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የእይታ ጥበብ ከሒሳብ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና በስዕል ግለጹ
2. የእይታ ጥበብን በመጠቀም በማህበራዊ ሳይንስ ምን አይነት ስዕሎችን ልንሰራ እንችላለን?
3. የ4ኛ ክፍል የሙዚቃ እና የሒሳብ ትምህርት ያላቸውን ዝምድና ግለጽ
4. ትያትር ልንሰራባቸው የምንችላቸው ታሪካዊ ክስተቶች ምን ምን ናቸው?

**መልስ**

1. ሂሳባዊ የሆኑ ስዕሎችን በመጠቀም የስዕልን እና የእይታ ጥበበን ዝምድና ያሳያሉ
2. ማህበራዊ ሳይንስን በተመለከተ ካርታ ፣ ሞዴሎችን ፣ ታሪካዊ ቦታዎችን እንዲሁም መሰል ነገሮችን ሊሰሩ ይችላሉ
3. ተማሪዎች ሙዚቃን በተመለከት ስለ መደመር ፣ ስለመቀነስ ፣ ስለማባዛ እና ስለ ማካፈል ሊናገሩ ይችላሉ
4. ትያትርን በተመጠቀም ስለ አካቢያቸው ንጉስ ፣ ስለ ታሪካዊ ቦታዎቻቸው እንዲሁም ባህላቸውን ሊገልጹ ይችላሉ

# ዋቢ መጽሀፍት

## የታተመ


1. Mihiretu wassie (2010 E.C). Drawing, Arba Minch College of Teachers' Education, student module አርባ ምንጭ


## መጽሀፍ


1. ሁሴን ጀማል (2001 ዓ.ም). ፕሮፌሽናል የካሜራ ጥበብ ፣ ነቢያት መጽሀፍት መደብር ፣ አዲስ አበባ
2. ጳውሎስ ኞኞ (1984). አጼ ምኒልክ ፣ አዲስ አበባ